# የኢፌዴሪ ፖሊስ ዶክትሪን



የሰላም ሚኒስቴር
MINISTRY OF PEACE

በኢትዮጵያ ፖሊስ የሪፎርም
ግብረኃይል የተዘጋጀ

መስከረም 2013 ዓ/ም
አዲስ አበባ

© መስከረም 2013 ዓ/ም የሰላም ሚኒስቴር

# የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አሕመድ መልእክት

ኢትዮጵያ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ የፖሊስ ተቋም ባለቤት ናት። ፖሊስ በዘመናዊ ቁመና ተደራጅቶ ግልጋሎት መስጠት ከጀመረ እንኳ ወደ መቶ ዓመት እየተጠጋ ነው። ነገር ግን ተቋማዊ አቅሙን እያሳደገ እንዲጎዘና ከሚመጣውና ከሚሄደው የመንግስት ስርዓት ጋር አብሮ እየፈረሰ ከዜሮ የሚጀምር እንዳይሆን ከማድረግ አንጻር በቂ ስራ ባለመሰራቱ ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት የጸዳና ሙያዊ አቅም ላይ የተመሰረተ የፖሊስ ተቋም ከመገንባት አንጻር ሰፊ ክፍተት ተፈጥሯል።


ይህን ነባራዊ እውነታ በመገንዘብ ፖሊስን ጨምሮ የደህንነትና የህግ አስከባሪ ተቋማትን የማሻሻል፣ የማጠናከርና ከፖለቲካ ወገንተኝነት የጸዳ የሙያ ተቋም ለመፍጠር የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። ይህም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፖሊስ ዶክትሪን ዘመኑን የሚመጥን የፖሊስ አደረጃጀትና የአሰራር አቅምና እሳቤ ለመታጠቅና የሃገራችን መጻዒ ተስፋን ሊያሰናክሉ የሚችሉ እንቅፋቶችን በሚያሻግር መልኩ የፖሊስ ሃይልን ለመገንባት የሚያስችል ነው።

የማህበረሰብ ስሪት እና የአኗኗር ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ መሄድ እና ከሌላው ዓለም ጋር ያለን መስተጋብር መጨመር ወንጀልን መከላከልንና መቆጣጠርን ውስብስብና አስቸጋሪ እያደረገው ይሄዳል። በዚህ ፈተና ውስጥ ሆኖ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በተቋማዊ ብቃቱ የላቀ፣ በአገልግሎት አሰጣጡ ምስጉንና አስተማማኝ አለኝታ የሚሆን ዘመን ተሻጋሪ የፖሊስ አገልግሎትን መገንባት ያስፈልጋል። የህዝባችንን ወቅታዊ ፍላጎቶችን የሚያረካ እና የወደፊት ራዕይን በተጨባጭ ማረጋገጥ የሚችል የፖሊስ ተቋምን የመገንባት ሥራ መሰረቱ ደግሞ ተቋሙ በግልጽ የሚመራበትና ከህዝብ የመነጨ የአስተሳሰብ ዳራ መንደፍ ነው።

ይህም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፖሊስ ዶክትሪን የሀገራችን ህዝቦች ከፖሊስ አገልግሎት ማግኘት ለሚፈልጉት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መደላድል የሚፈጥርና በሃገራችን የህጎች ሁሉ የበላይ ከሆነው ህገ-መንግስት እሳቤ በመነሳት የተዘጋጀ ሰነድ ነው። ለዚህ ሀገራዊ ሰነድ ተግባራዊነት የሚረዱ የማስፈጸሚያ ዝርዝር ሰነዶች በህብረተሰብና በፖሊስ መካከል ያለውን ውል በተሻለ መሠረት ላይ የሚያስቀምጡ ይሆናሉ።

በአጠቃላይ የህግ ማስከበርና የጸጥታ ተቋማትን የአስተሳሰብ፣ አደረጃጀትና አፈጻጸም አቅም በማሳደግ የጸና መሠረት ላይ ማቆም የዘላቂ ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ መገንቢያ ሁነኛ መሳሪያዎቻችን ናቸው። የዚህ ዶክትሪን መዘጋጀት ለዘመናት ሲናፈቅ የነበረውን ለሕገ-መንግስታዊ ስርዓት ዘብ የሚቆም ፖሊስ ለማደራጀት የሚረዳ ሲሆን በዚህ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለስራ ሲቀርብ በሀገራችን የፖሊስ ታሪክ የመጀመሪያው በመሆኑ ደስታ ይሰማኛል።

የኢትዮጵያ መንግሥትም የፖሊስ ተቋምን እድገት፣ ነፃነትና ክብር የማረጋገጥ ሀላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ያለውን ጽኑ አቋም በተግባር ማረጋገጫ የሆነው ይህ የፖሊስ ሪፎርም አካል የሆነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፖሊስ ዶክትሪን ተግባራዊ ሆኖ የሚፈለገው ውጤት እንዲገኝ ሁሉም አካል የሚጠበቅበትን ሃላፊነት እንዲወጣ ከአደራ ጭምር ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።



ዐብይ አሕመድ (ፒኤች.ዲ)
ጠቅላይ ሚኒስትር

# ክብርት ወ/ሮ ሙፍሪሃት ካሚል
# የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር


የፖሊስ ተቋሞቻችንን በአመለካከት፣ በመዋቅርና በአፈጻጸም የማዘመን ሂደት ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ይህ - የኢፌዴሪ ፖሊስ ዶክትሪን - ሰፊው የህብረተሰባችን ክፍል ረዘም ላለ ጊዜ ሲያቀረበው ለነበረው ፍትሀዊና ህጋዊ ጥያቄ በተገቢውና በተሟላ መልኩ ለመመለስ ታልሞ የተዘጋጀ ነው። ከጥንስሱ ጀምሮም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ መንግስታዊ የሆኑ የፌዴራልና የክልል ቢሮዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ሙሁራንን እና ቀደምት የፖሊስ ሀይላችን አመራርና አባላትን እይታ በጥልቅ ያካተተ፣ ከህዝብ ለመነጨ ጥያቄ ህዝባችን ባፈለቀው መልስ ላይ በመመርኮዝ የተሰናዳ ሰነድ ነው።

በሀገራችን የፖሊሳዊ አገልግሎት ጅማሮ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ እና በፍትህ ስርዓት ውስጥ ከመጀመሪያው ረደፍ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ውስጣዊ አደረጃጀቱ አሰራሩ እና የሚሰጣቸው አገልግሎት ዓይነቶች ከማህበረሰቡ ነባራዊ እውነታ ቀጥተኛ ቁርኝት ነበራቸው ለማለት አያስደፍርም። ይልቁንም አስተሳሰቦቹ በየጊዜው ወደ ስልጣን ከመጡ መንግስታት አጠቃላይ ባህርይ፣ የአስተዳደር ዘይቤና የፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር እንዲቃኙ በመደረጉ አገልግሎቱ ህዝባዊ አመኔታ እየቀነሰ እና ዓለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነቱም ዝቅተኛ ሆኖ ቆይቷል።

ከዚህ በላይ የተገለጹትን ዘርፈ ብዙ ማነቆዎች በመፍታት ፖሊሳዊ አገልግሎትን ከኢትዮጵያ ነባራዊ እውነታ የመነጨና ዓለምአቀፍ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረገ ሆኖ እንዲደራጅ ለማድረግ ይህ በአገራችን ታሪክ የመጀመሪያው እና በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ የሚሆን "የኢፌዲሪ ፖሊስ ዶክትሪን" ተዘጋጅቷል። ዶክትሪኑ የፖሊስን የማህበረሰብ አገልጋይነት፣ የህግ አስከባሪነትን እና የወንጀል መንስኤዎችን ተቆጣጣሪነት ብቃት ለማሳደግ በሚረዱ አስተሳሰቦች ተቃኝቷል። ለነዚህ አስተሳሰቦች ተግባራዊነትም ፖሊስ ከማንኛውም የፖለቲካ አስተሳሰብና ተጽእኖዎች ነጻ፣ በአስተሳሰቡ ኢ-ወታደራዊ፣ በአሰራሩ ያልተማከለና አሳታፊ ወይም ዴሞክራት እንዲሆን ተደርጓል።

ዶክትሪኑ የኢትዮጵያ ፖሊስ የላቀ ሙያዊ ነጻነትን፣ ምሉዕነት/ታማኝነትን፣ ብዝሀነትን (አካታችነት) እና ሰብዓዊ መብት ማክበርን መለያ እሴቶቹ አድርጓል። በዚህ ዶክትሪን መሰረት ፖሊስ የሚመራው በፖሊስ ሣይንስ ዕውቀት ነው። ይህ ዕውቀት የሚገኘው ከፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ነው። የነዚህ እና ሌሎች በዚህ ዶክትሪን የተካተቱ ጥልቅ የአስተሳሰብ አምዶች ኢትዮጵያዊ ሰላምና አብሮነት የተገነባባቸው ማህበራዊ ሀብቶችና መስተጋብሮች፣ እሴቶችና ብሄራዊ ጥቅሞቻችን እና ዓለም አቀፍ አዳጊ ሁኔታዎችና አዝማሚያዎች ናቸው። ይህም የአገራችንን ፖሊስ አገልግሎት ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ የሚያደርግና ዓለም ከደረሰበት ደረጃ የሚያደርሰው ይሆናል። በሌላ በኩል ተቋማዊ ነጻነቱን በማረጋገጥ ረገድም የህዝብን ቀጥተኛ ተሳታፊነትንና ባለቤትነትን የሚያሰፋ ሲሆን የፖሊስ ህልውናም የሚወሰነው በህዝብ ይሁንታና እርካታ እንዲሆን ያደርጋል።

በአጠቃላይ የኢፌዲሪ ፖሊስ ተቋምና አገልግሎት የማቋቋሚያ አዋጆች፣ ዝርዝር ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶችና ስትራቴጂዎች ከዚህ ዶክትሪን ብቻ የሚቀዱ ይሆናል። ከዚህ ዶክትሪን አስተሳሰብ ውጪ የሚሰሩ ተግባራት በሙሉ የተከለከሉ ናቸው። በመጨረሻም ለዶክትሪኑ ተግባራዊነት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ መንግስታዊ ተቋማት፣ የሲቪል ማህበራት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የፖለቲካ ደርጅቶች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የሃይማኖትና እምነት ተቋማት ወዘተ በቀጥታ በባለቤትነት በመሳተፍ፣ ተገቢውን ጥበቃ በማድረግና በማሳደግ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በታላቅ አክብሮትና ሀገራዊ ኃላፊነት እያሳሰብሁ ይህ የፖሊስ ዶክትሪን ከመስከረም 2013 ዓ/ም ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል መወሰኑን አበስራለሁ።




መስከረም 2013 ዓ/ም

# የክቡር ኮሚሽነር ጄኔራል መልዕክት

የፖሊስ ሙያ በባህሪው ከአገር አልፎ አህጉራዊና አለምአቀፋዊነት ይዘት ያለው ነው። አገልግሎቱም በየትኛው ሀገርና ቦታ ሞያው ወጥነትና ተመሳሳይነት የሚታይበት፤ የሚኖርበትንና የሚሰራበትን ማህበረሰብ ችግር የራሱ አድርጎ የማየትና ለህብረተሰቡ ፍላጎትና ጥቅም ተገዥ መሆንን የሚጠይቅ ነው።

የፖሊስ የአገልጋይነት መንፈስ በየጊዜው የፖሊስ ሳይንስ እድገት በሚጠይቀው መልኩ ራስንና ተቋምን እያበቁ መሄድን የሚፈልግ ነው። ይህን ለማድረግ ግለሰባዊና ተቋማዊ ነፃነቱ ተጠብቆ ለህገመንግስትና እሱን ተከትሎ ለሚወጡ ህግች፤ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም ለህብረተሰብ ጠቃሚ ባህልና ወጎች ተገዥ መሆንን ይጠይቃል።

በፖሊስ አባላትና በተቋሙ ከየትኛውም አካል ሊደርሱ የሚችሉ ጣልቃ ገብነትን የሚከለክል፣ በሀገሪቱ በተለያየ ጊዜ መንግስታዊ ስልጣንን በሚይዙ ፓርቲዎች ርዕዩት - አለም እየተቃኘ የማይለወጥ ወይም ተፅዕኖ ስር የማይወድቅ ተቋማዊ ቁመና ሊኖረው ይገባል፡ ፡ በተጨማሪም ፖሊስ ነፃ ሆኖ በሞያውና በሀገሪቱ ህገ በገለልተኝነት የሚመራበት ግልጽ ራዕይና ተልዕኮ ያለው እንዲሆንና ከትውልድ ትውልድ እየተሻሻለ የሚሸጋገር ተቋም አድርጎ መገንባት ያስፈልጋል።

ስለሆነም ውጤታማና አገልጋይ ተቋም ለመገንባት በውስጡ በጠንካራ የፖሊሳዊ ሰብዕና የተገነባ የሰው ሃይል መፍጠር የሁሉም ነገር መጀመሪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። እነዚህን ሁሉ መሰረታዊ ሀሳቦች ተቋማዊ ባህል አድርጎ ለመቀጠል አባላቱ ሊመሩበት የሚገባ ግልፅነት ያለው ፍልስፍና ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፖሊስ ዶክትሪን በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጅቷል። ዶክትሪኑ የዘመናት ተቋማዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችለን፣ ፖሊስን ዘመናዊና ተደራሽ የሚያደርግ እና ከማህበረሰቡ የላቀ ይሁንታ ለማግኘት የሚረዳን በመሆኑ እንኳን ደስ አለን ለማለት እወዳለሁ።

በመጨረሻም መላው የሀገራችን የፖሊስ አባላትና አመራሮች ሰነዱን የሁሉም ነገራችን መነሻና መድረሻ አድርገን እንድንጠቀምበት እና ለአፈፃፀሙ ውጤታማነት ሁላችንም የድርሻችንን እንድንፈፅም ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ።



እንዳሻው ጣሰው
ኮሚሽነር ጀነራል

# ክፍል አንድ

**መግቢያ:ታሪካዊ ዳራ፣ ........................................ 7**

**የኢፌዴሪ ፖሊስ ዶክትሪን መነሻ፣ አስፈላጊነትና ዓላማ ................ 7**

1.1 መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

1.2 ታሪካዊ ዳራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

1.3 የዶክትሪኑ አጠቃላይ መነሻ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

1.4 የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . 11

1.5 የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ . . . . . . . . 12

# ክፍል ሁለት

**የፖሊስ ዶክትሪን ጽንሰ-ሃሳቦች እና የአገራት ልምዶች፣ ............... 13**

2.1. የፖሊስ ዶክትሪን ጽንሰ-ሃሳቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . 13

2.2 በፖሊስ ዶክትሪን የአገራት ልምዶች . . . . . . . . . . . . . . . . 14

# ክፍል ሶስት

**የኢፌዲሪ ፖሊስ ዶክትሪን መሰረታዊ ምልከታዎች እና እሴቶች........ 15**

3.1. የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን መነሻ ሃሳቦች እና ምልከታዎች . . . . . . . . 15

3.2. የኢትዮጵያ ፖሊስ የሚመሰረትባቸው እሴቶች . . . . . . . . . . . . . 19

3.2.1. ሙያዊ ብቃት (Professionalism) . . . . . . . . . . . 20

3.2.2. ምሉዕነት/ታማኝነት (Integrity). . . . . . . . . . . . 21

3.2.3. ብዛሀነትን ማክበር (አካታችነት) (Respect for Diversity) 22

3.2.4. ሰብዓዊ መብት ማክበር (Respect for Human Rights) . . 22

# ክፍል አራት

**የኢፌዲሪ ፖሊስ የአስተሳሰብ እና የድርጊት መርሆዎች ................ 24**

4.1. የፖሊስ ተቋማት ትኩረት ህግጋት እና አደረጃጀት ዶክትሪን፣ . . . . . . . 24

4.1.1. የኢፌዲሪ ፖሊስ አሰራርን የሚወስኑ ህጎች እና ደንቦች፣ . . . . . . . . 24

4.1.2. የኢ.ፌዲ.ሪ ፖሊስ ተቋማት አደረጃጀት ቅርፅና ይዘት፤ . . . . . . . . . . 26
4.2. የፖሊስ የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዶክትሪን፤ . . . . . . . . . . . . 28
4.2.1 የፖሊስ የሰው ሐብት ልማት፣ ምደባና አስተዳደር፤ . . . . . . . . . . 29
4.2.1.1 የፖሊስ ሰው ሐብት ልማት፤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
4.2.1.2 የፖሊስ የሰው ሀብት ምደባ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32
4.2.1.3 የፖሊስ ሰው ሀብት አስተዳደር፤. . . . . . . . . . . . . . . . . 33
4.2.2. የፖሊስ ማዕረግ አሰጣጥና የዕዝ ጠገግ (Chain of Command)፤ . . 33
4.2.3. የፖሊስ ስነ- ምግባርና ስብዕና (Police Ethics) ግንባታ፤. . . . 34
4.3. የፖሊስ ተቋማት የግንኙነት ዶክትሪን፤ . . . . . . . . . . . . . . . . 35
4.3.1. በፖሊስ ተቋምና በህብረተሰቡ መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት፤ . . . . . 36
4.3.2. የፖሊስ ተቋማት ከመስተዳድር አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፤ . . . . 37
4.3.3. የፖሊስ ተቋማት ከፍትህና የዳኝነት አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፤ . . . 39
4.3.4. የፖሊስ ተቋማት ከሌሎች የፀጥታ አካላትጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፤ . . . . 39
4.3.5. ፖሊስ ከውጭ አገራትና አለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅቶች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 39
4.3.6. የኢትዮጵያ ፖሊስ የመገናኛ ብዙኀን አጠቃቀም፤ . . . . . . . . . . 40
4.4. የፖሊስ ተቋማት ፖሊሳዊ ተግባራት፤ የመሰረታዊ ግብዓቶችና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ዶክትሪን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 41
4.4.1. የፖሊስ የዕለት ከዕለት ፖሊሳዊ አሰራር፤ . . . . . . . . . . . . . . 41
4.4.2. የፖሊስ የኃይል አጠቃቀም፤. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 42
4.4.3. የፖሊስ ስራ ማስፈፀሚያ መሰረታዊ ግብዓቶች አቅርቦትና አጠቃቀም፤ . . . 42
4.4.4. የፖሊስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖለጂ (ICT) አቅርቦት እና አጠቃቀም፤ . . . 43

## ክፍል አምስት

**ማጠቃለያ ........................................................ 44**

# ክፍል አንድ

## መግቢያ:ታሪካዊ ዳራ፣

## የኢፌዴሪ ፖሊስ ዶክትሪን መነሻ፣ አስፈላጊነትና ዓላማ

### 1.1 መግቢያ

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት ውስጥ በተካተቱ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ በመመስረት ለፌዴራል መንግስቱ የተሰጡ ህገ መንግስታዊ ኃላፊነቶችንና ስልጣኖችን ተግባራዊ ለማድረገና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ከሆኑ የፍልስፍና ማጠንጠኛ ሰነዶች ውስጥ አንዱ የፖሊስ ዶክትሪን ነው፡፡

ፖሊስ በአንድ ሀገር ፍትህን ለማስፈን በሚደራጁ የፍትህ ስርአቶች ውስጥ የሚገኝ ሆኖ የፀጥታ ችግሮችንና ወንጀሎችን አስቀድሞ የመከላከል፣ ከተከሰቱም የመቆጣጠርና የመመርመር፤ የትራፊክ ደንቦችን የማስከበር እና ለማህበረሰቡ ድጋፍ የመስጠት አገልግሎቶችን (Police Service) ለማቅረብ በህግ የሚቋቋም ተቋም ነው፡፡ ይህም በአንድ አገር የፍትህ ስርዓት ውስጥ ከመጀመሪያው ረድፍ ላይ የሚገኝ እና ለህዝብ ቅርብ የሆነ ተቋም እንዲሆን አድርጎታል ፡፡ ፖሊስ ከህዝብ ጋር ባለው የዕለት ከዕለት ግንኙነት እና ቅርበት የተነሳም የአገልግሎቱ አስፈላጊነት ከሌሎች የመንግስት ተቋማት አንጻር ሲታይ እጅግ ከፍተኛም ነው፡፡

የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ረገድ የሚወሰዱ የፖሊስ ተግባራት ከማህበረሰቡ ማህበራዊ ሁኔታዎች፣ የስነልቦና ይዘትና አጠቃላይ አውድ አንጻር የተቃኙ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ ስለዚህም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የፖሊስ እሴቶችና መርሆችን ያገናዘበ እንዲሁም ለዘመናችን ማህበረሰብ የሚመጥን ፕሮፌሽናልና ዘመናዊ ፖሊስን ማደራጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡ የአገራችን ህዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ፍትህ ያለአድሎ እንዲከበር እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብልጽግናው በዘላቂነት እንዲረጋገጥ ፖሊሳዊ ተቋሞችንና አገልግሎቶችን ማጠናከርና አደረጃጀታቸውን ፕሮፌሽናል ማድረግ መሰረታዊ የሆነ ኃላፊነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

የፖሊስን ዘመን ተሻጋሪ ተቋምነትን በማረጋገጥ ቀጣይነቱን አስተማማኝ ለማድረግ የኢፌዲሪ ፖሊስ የሚመራበት ግልጽ የፍልስፍና ወይም የዶክትሪን ባለቤት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዶክትሪን የኢፌዴሪ ፖሊስ ማለት በሀገራችን የግዛት ወሰን ውስጥ የሚገኙ የፖሊስ ተቋማትን ይይዛል ፡፡

ይህም በተለያየ ጊዜ ወደ መንግስት ስልጣን በመጡ መንግስታት የተሰሩ በጎ የፖሊስ ተግባሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩና እኩይ ተግባራቶችም እንዲታረሙ የሚያደርግ ነው፡፡ የዶክትሪኑ መኖር ዘመን ተሻጋሪ ፖሊስን በመገንባት ረገድ ሚዛን ደፊ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህም ወደ ስልጣን የመጣው ሁሉ እንደፈለገው እያፈረሰ በራሱ ልክ የሚሰፋው የፖሊስ ተቋም እንዳይሆን ይከላከላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለዶክትሪን መኖር እንደ መነሻነት የተገናዘቡት በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ የጥናትና ምርምር ውጤቶች የተሰጡ አስተያየቶች ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ የፖሊስ ስትራቴጂክ ፍኖተ ካርታ ፣ የተለያዩ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች፣ ስታዳርዶችና በፖሊስ አሰራር ላይ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚረዳ ወጥ የፖሊስ ፍልስፍና ወይም መሪ ሀሳብ አስፈላጊ መሆኑ ላይ ከአብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች ሀሳብ የተሰጠበትና መግባባት የተደረሰበት መሆኑ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት መሰረታዊ ጭብጦች በመነሳት በአለም አቀፍ የፖሊስ ተግባር ውስጥ እንደ ቁልፍ ተልእኮ የሚወሰዱትን፣ ማለትም ማህበራዊ አገልግሎትን መስጠት (Social Service) ፣ ህግን ማስከበር (Law Enforcement) እና ወንጀል መቆጣጠርን (Crime Control) የተልዕኮው ማእከል በማድረግ ለአፈጻጸማቸው የሚረዱ ገዥ የፍልስፍና መነሻዎች እንዲኖራቸው ማድረግ የወቅቱ ጥያቄ ሆኗል።

ይህም ከማንም የፖለቲካ ድርጅቶች ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆኖ በፖሊስ ሳይንስ፣ ዕውቀት እና ስነ-ምግባር ብቻ የሚመራ ኢትዮጵያዊ የፖሊስ ተቋምን በመገንባት ሰላምንና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊስ ተቋምን እውን ለማድረግ ይረዳል። በፖሊስ ላይ የሚነሱ የህዝብ ቅሬታዎችን በማስወገድ ህዝባዊነቱንና ተቀባይነቱን ማረጋገጥ ያስችላል ። በዚህ ዶክትሪን የህዝብ ሉአላዊነት የሚረጋገጥበትና የፖሊስና ህዝብን ግንኙነት የሚያሻሽሉ ሀሳቦች ተካተውበታል። ተቋሙም በህዝብ ይሁንታና የአገልግሎት ርካታ የሚቀጥልና የሚመዘን ያደርገዋል።

ይህ የፖሊስ ዶክትሪን ሰነድ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍል አንድ መግቢያ የዶክትሪኑ መነሻ፣ አስፈላጊነት እና ዓላማን ይዟል። ክፍል ሁለት የፖሊስ ፍልስፍና ወይም የዶክትሪን ጽንሰ-ሃሳቦች እና የአገራት ልምዶችን ጠቅለል አድርጎ ይዟል። ክፍል ሶስት ደግሞ የኢፌዴሪ ፍልስፍና ዋና ዋና ምልከታዎችን እና እሴቶችን ሲይዝ ክፍል አራት የኢፌዴሪ ፖሊስ የአስተሳሰብና ድርጊት ገዥ መርሆዎችን አካቷል ።

## 1.2 ታሪካዊ ዳራ

ከህብረተሰብ የዕድገት ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው የማህበራዊ ግንኙነትንና እንቅስቃሴን ሰላማዊ ለማድረግና የግለሰቦችን ባህርይ ለመግራት ሲባል በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ህጎችና ድንጋጌዎች ሲወጡ ቆይተዋል። በየአገራቱ አጥፊዎችን ለመቅጣትና ለማረም ደግሞ የተለያዩ የመቅጫ ዘዴዎችን ይተገብሩ እንደነበረም መረዳት ይቻላል።

ጥንታዊው ህብረተሰብ ከማህበረሰብ ልማድና ወግ ወጣ ያሉና በማህበረሰብ አጠቃላይ ሰላምና ጤናማ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ አጥፊዎችን ለመቆጣጠር ሲል ህግን ማውጣት የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት 2300 ዓመተ ዓለም ላይ እንደነበረ ከድርሳናት ማረጋገጥ ይቻላል።

በሀገራችን የፖሊሳዊ አገልግሎት ጅማሮ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ቢሆንም ዘመናዊ የፖሊስ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በህግ የተቋቋመው በ1930ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ አካባቢ ነው፡ ፡ ይህ የፖሊስ ተቋም ውስጣዊ አደረጃጀቶቹ እና የሚሰጣቸው አገልግሎት ዓይነቶች በየጊዜው ወደ ስልጣን ከመጡ መንግስታት አጠቃላይ ባህርይ፣ የአስተዳደር ዘይቤና የፖለቲካ አስተሳሰብ (Political Ideology) በመነጩ ሀሳቦች ቅኝት የተቀመሩ እንደነበርም ጥናቶች ያሳያሉ።

በዚህ የተነሳ የአገራችን ፖሊስ ተቋም ከፖሊሳዊ ሙያ በወጣ መልኩ ከመንግስታቱ ባህርያት የመነጩ ስሞች ሲሰጡት ቆይቷል። ይህም ተቋሙንና በተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ የፖሊስ አባላትን ጭምር ዋጋ አስከፍሏቸዋል።

ይህም ሆኖ በፖሊስና ህዝብ መካከል በሚደረግ ግንኙነት አጋርነትን መመስረት እና በኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ፍልስፍና ላይ መሰረት ያደረገ የፖሊስ አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ በየመንግስታቱ የተደረጉ ጥረቶች በአዎንታዊ መልኩ ልምድ የሚወሰድባቸው ናቸው ።

በየትኛውም ሀገር ህዝብ የፖሊስን አባል ሳያይ ወይም የተለያየ ድጋፍ ፍለጋ ሳይመጣ የሚዉልበት ጊዜ የለም። ፖሊስም የሰው ልጅ በሚገኝበት ቦታ እና አንዳንዴም ለመኖር አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች ሁሉ መገኘቱ ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ትስስር ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።

ስለሆነም የአገራችን ፖሊስ ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ ባህሪይ ባለው የፖሊስ ተልዕኮ በመታጀብ የዘመኑ የፖሊስ አገልግሎት የሚጠይቀውን ወንጀልን ቀድሞ የመከላከል (Proactive Policing) ሞዴል ወይም ስትራቴጂ የስራው ማዕከል በማድረግ ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን በመቀነስ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ እና ተአማኒ መሆን ይገባዋል። ለዚህ ግብ መሳካትም የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ፍልስፍና መሪ የፖሊስ ሞዴል መሆን አለበት። የማህበረሰብን ችግር በማህበረሰብ ተሳትፎ መለየትና በጋራ መፍታት የማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ላይ አዎንታዊ እና ትርጉም ያለዉ ለዉጥ ለማምጣት ቁልፍ ሚና አለዉ።

ስለዚህ በፖሊስ ስራ ውስጥ ዓለም አቀፍ ስምምነት የተደረሰባቸውን ፖሊሳዊ ተልእኮዎችና ሌሎች ሀገር በቀል የሆኑ ልምዶችን በተገቢው መንገድ በመገንዘብ፣ ተጠሪነትን ለህዝብና በህዝብ ለተመረጠ መንግስት በማድረግ፣ እንደዚሁም በዘመኑ የፖሊስ ፍልስፍና ሚዛን በሚደፋው የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ስትራቴጂ አወቃቀርን በማስተካከልና አስተሳሰብን በማነጽ የአገልግሎት ብቃትን ማሳደግ ይገባል።

የፖሊስ ዶክትሪን መኖር ሙያዊ ነጻነትን ከማረጋገጥ በላይ ፖሊስነት ድንበር አልባና በዕውቀት የሚመራ በማህበራዊና ተፈጥሮ ሳይንስ ላይ የተመሰረተ መሆኑን በማረጋገጥ በህዝብ ተቀባይነትን ለማግኘት የሚረዳ ሰነድ ነው። ይህም ከስርዓቱ ለውጥ ጋር አብረው በሚወለዱ የአይዲኦሎጂ ልዩነቶች እየፈረሰ የሚገነባ ሳይሆን ከዘመን ዘመን የሚሻገር የፖሊስ ስርዓትን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ነው ።

## 1.3 የዶክትሪኑ አጠቃላይ መነሻ

በየትኛውም አገር የፖሊስ ተልዕኮ ትኩረት ከሚሰጣቸው የፖሊስ ስትራቴጂዎች ውስጥ በቅድመ ወንጀል መከላከል (Proactive Policing) ዘዴ ለወንጀል መፈጠር ምክንያት የሚሆኑ የማህበረሰብ ችግሮችን መፍታት፣ ከተፈጸሙም በፖሊሳዊ ሳይንስና የወንጀል ምርመራ ዘዴ በማጣራት ለህግ ማቅረብ ቢሆንም የአካባቢን ጸጥታ ቀጣይነት ለማረጋገጥ እስከ የማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ ለውጥ ማምጣት ድረስ የሚሄዱ ተግባራትን የስራው አካል ማድረግ አለበት ፡፡

ለዚህ ስኬት መሰረት የሚሆኑ ግብዓቶች ማቅረብና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ ፖሊሳዊ እሳቤዎችን በአግባቡ መሰነድ ህብረተሰቡ ተደራሽ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችለዉ በመሆኑ የፕሮፌሽናል ፖሊስ ሀይል ግንባታ ለአፍታም ቸል የማይባል የፖሊስ ተቋማት የሙያ ግዴታ ነው፡፡

የብዙ የዓለም ሀገራት ፖሊስ ልምዶች እንደሚያሳዩት ፖሊስ በአገልግሎት አሰጣጡ ተመራጭ እና የላቀ እንዲሆን የሚያደርግ በፖሊስ ልክ የተቀረጸ ፍልስፍና ወይም ዶክትሪን እንዳላቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ የፖሊስ ዶክትሪን በሀገር አቀፍ ደረጃ ጠንካራና በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ዘመናዊ የፖሊስ ተቋም በመገንባት የፖሊስ አገልግሎትን በውጤታማነት ለህብረተሰቡ ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ ፍልስፍናዎችንና እሳቤዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ የያዘ ሰነድ ነው፡፡

በዚህ የአስተሳሰብ ማእቀፍ ውስጥ የፖሊስ ዶክትሪን በየደረጃው መግባባት ከተደረሰበት በኋላ ፖሊሳዊ አዋጆች፣ ዝርዝር ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ አሰራሮች፣ የትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርቶች፣ ስታንዳርዶች፣ ማንዋሎች ወዘተ…ይህንን መሰረት አድርገው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ አስገዳጅነት ያለው ሰነድ ይሆናል፡፡ በዚህ መነሻም የዶክትሪኑ የተፈፃሚነት ወሰን በሁሉም የሃገሪቱ የፖሊስ ተቋማት፣ አባላት፣ አገልግሎት እና ስርዓት ላይ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም ዶክትሪን በተቋማዊ አስተሳሰብ ላይ ተቀራራቢ ግንዛቤ እንዲኖር በማድረግ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች፣ የጥናትና ምርምር ስልቶች፣ እንዲሁም የወንጀል መከላከል፣ ምርመራና የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ስትራቴጂዎችን ለመንደፍ መነሻ እና ማጣቀሻ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ዶክትሪኑ የፖሊስ አባላት አዲስ አስተሳሰብ እንዳይኖራቸዉ በር የሚዘጋ ተጽእኖ እንዳይኖረዉ መጠንቀቅ የሚያስፈልግ ሲሆን ይልቁንም ከአዳጊ ሁኔታዎች ጋር እያደገ እንዲሄድ አዳዲስ ሃሳቦችን ለማፍለቅና ለመቀበል የሚያስችል የአስተሳሰብ ማዕቀፍ የሚፈጥር እና በተወሰነ አመትም ምክረ ሀሳቦች እየቀረቡ ሊሻሻል ይገባዋል፡፡

የፖሊስን ስራ ውጤታማ ለማድረግ በፖሊስ ሙያ ሰልጥነው ማረጋገጫቸውን በህግ ዕውቅና ካላቸው የፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋማት ያገኙ የፖሊስ አባላትን በብዛትና በጥራት ማፍራት ይጠይቃል፡፡ ፖሊስ

ከሰው ሀይል ልማት ፕሮግራሞች በተጨማሪ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ውጤት በሆኑ የፖሊስ ስራ ደጋፊ ግብዓቶችና መሳሪያዎችም ሊደራጅ ይገባዋል።

የፖሊስ ዶክትሪን ምሰሶዎች ተብለው ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው በዋነኛነት የላቀ ሙያዊ ብቃት፣ የኦፕሬሽን ነጻነት፣ ምሉዕነት፣ የዜጎችን የአስተሳሰብ፣ የማንነትና የእምነት ብዝሀነት እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፣ ለህዝብ ይሁንታ መገዛትና አለማዳላት ናቸው። የዚህ ዶክትሪን መነሻዎች ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኙ የጥናትና ምርምር ውጤት የሆኑ ግኝቶች ሲሆኑ ዓላማውም በግኝቶቹ መነሻነት የታዩ ክፍተቶችን መሙላት እና የፖሊስ ፕሮፌሽናሊዝምን አስተሳሰብ ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ የኢትዮጵያን ህዝብ የፍትህ ጥማት ማርካት ነው ።

ከዚህ ዓለም አቀፍ ባህሪ ካለው ፖሊሳዊ ተልዕኮ አኳያ የሀገራችን ህዝብ ሰላምና ደህንነት እንዲከበር እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብልጽግናው እንዲረጋገጥ ፖሊሳዊ ተቋሞችና አገልግሎቶች የሚመሩበት ግልጽ ዶክትሪን ሊኖራቸው ይገባል። ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ጥቅሞች ለማግኘት ሲባል የኢፌዴሪ ፖሊስ የሚመራበት ይህ ዶክትሪን ተዘጋጅቷል።

## 1.4 የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን አስፈላጊነት

በርካታ አገራት በፖሊስ መሰረታዊ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች መነሻ በግልጽ ፍልስፍና ስለሚመሩ ተቋማቱ መሰረታዊ የፖሊስ እሴቶችንና መርሆዎችን ጠብቀው በትውልዶች ቅብብሎሽ ዘመናትን የሚሻገር ተቋም አድርገውታል ።

በአገራችን ዘመናዊ የፖሊስ ተቋም ምስረታ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም በየዘመኑ በነበሩ መንግስታት የነበሩ የፖሊስ ተቋማት ለመንግስታቱና ለአገዛዝ ስርዓታቸው የቅርብ አገልጋይ እንዲሆኑ ተደርገው የተቃኙና በአጠቃላይ የመንግስታቱን ባህሪይና ፖለቲካዊ ቅርጾቻቸውን እንዲላበሱ የተደረጉ ናቸው።

በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያለው የሀገራችን የፖሊስ ተቋም፣ አባል፣ አገልግሎቱና የአሰራር ስርዓቱ በገዢው የፖለቲካ ፓርቲ ጣልቃ ገብነትና ተጽዕኖ ስር በመውደቁ ግልጽ የሆነ ፖሊሳዊ ዶክትሪን የሌለው፣ ሙያዊ ብቃቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ የሄደ፣ በስነ ምግባር ችግሮች የተተበተበ ሆኖ እንዲቆይ አድርጎታል።

በዚህም ተቋማዊ የሰው ኃይል ልማቱ፣ የማዕረግ፣ የዕዝ ሰንሰለትና የዕድገት አሰጣጥ አሰራሩ፣ አደረጃጀቱ እና የሎጅስቲክስና ቴክኖሎጂ አቅርቦቱና አጠቃቀሙ በአጠቃላይም የፖሊሳዊ ተልዕኮዎች አተገባበሩ ኋላቀር ሆኖ ቆይቷል።

እነዚህን ተቋማዊ ችግሮች ከመሰረቱ በዘላቂነት መፍታትና የፖሊስ ተቋማት በተለያየ ጊዜ ወደ ስልጣን በሚመጡ መንግስታት ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ስር እንዳይወድቁ ማድረግ ተገቢና አስፈላጊ ነው፣

፡ በዚህ አስተሳሰብ የሀገራችን የፖሊስ አገልግሎት በፖሊሳዊ ሙያ ብቻ እየተመራ ለማህበረሰቡ ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ህገ መንግስቱን፣ የማህበረሰቡን ነባራዊ ፍላጎት እንዲሁም ሀገራዊ፤ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችንና አዝማሚያዎችን መነሻ ያደረገ የፖሊስ ዶክትሪን ሊኖረን ይገባል።

በዚህ መሰረት የአገራችን ፖሊስ የሚመራበት አንድ አገራዊ የመግባቢያ ሰነድን በማዘጋጀት ፖሊስ በህግ ማስከበር ረገድ በየደረጃው ተቀራራቢ አፈጻጸም እንዲኖረው ለማስቻል እንዲሁም ዓለማቀፋዊ ይዘት ያለው፣ ዘመናዊ፣ ሙያዊ ነጻነቱን ጠብቆ የሚሰራና ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ አስፈልጓል።

በተጨማሪም በሀገር አቀፍ ደረጃ የፖሊስ አገልግሎት ተቀራራቢ እንዲሆን በማድረግ በየጊዜው እያደገና እየተሻሻለ የሚሄድ የፖሊስ ተቋም ለመገንባትና በትውልዶች ቅብብሎሽ እየዳበረና እየተገነባ የሚሄድ ፖሊስ ተቋምና አገልግሎትን እውን ለማድረግ የኢፌዲሪ የፖሊስ ዶክትሪንን ማዘጋጀት አስፈልጓል።

## 1.5 የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎች፣

### ጠቅላላ ዓላማ

የኢፌዲሪ ፖሊስ ዶክትሪን ዋና ዓላማ የአገራችን ህዝቦች ሰላም፣ ደህንነትና ፍትህ እንዲከበር እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብልጽግናቸው በዘላቂነት እንዲረጋገጥ የፖሊስ ተቋማትንና የአገልግሎት አሰጣጥን ከአገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም አካባቢያዊና ዓለምአቀፍ ለውጦች ጋር ተጣጥመው ሊሄዱ የሚችሉ በማድረግ ኢትዮጵያዊ የሆነ የፖሊስ ተቋምን መገንባት እና ሰላምንና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ነው ።

### ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ. የኢትዮጵያ ፖሊስ ተልዕኮዎች ቋሚ የፍልስፍና መነሻዎች እንዲኖራቸው በማድረግ ከፖለቲካ ነጻና፤ ሙያዊ ነጻነቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲቀጥል አንድ የሚመራበት ፍልስፍና ወይም ዶክትሪን ባለቤት እንዲሆንና ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡ ጣልቃ ገብነቶችንና እንቅስቃሴዎችን ለመከላከልና ለመግታት፣

ለ. ፖሊሳዊ አገልግሎቶች በፖሊስ ሳይንስና ዕውቀቶች የሚመሩ ሆነው ከታች ወደ ላይ በሚፈስ የፖሊስ እና የህዝብ ግንኙነት ላይ መሰረቱን ያኖረ ፕሮፌሽናል ፖሊስን ለመገንባት፣

ሐ. ለሌሎች የፖሊስ ህጎች ፣ ደንቦች ፤ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች፣ እንዲሁም የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ፣ እና

መ. በተለያዩ ጊዜያት ከሚከሰቱ የመንግስታት ባህርያት ጋር አብሮ እየወደቀ የሚነሳ ወይም እየፈረሰ እንደ አዲስ የሚገነባ ሳይሆን በትውልድ ቅብብሎሽ ከዘመን ዘመን እየተሸጋገረ የሚሄድ የፖሊስ ተቋም ግንባታን መሰረት መጣል ነው፣

# ክፍል ሁለት

## የፖሊስ ዶክትሪን ጽንሰ-ሃሳቦች እና የአገራት ልምዶች፣

### 2.1. የፖሊስ ዶክትሪን ጽንሰ-ሃሳቦች

በፖሊስ ተቋምና አገልግሎት ዙሪያ ከተጻፉ ሰነዶች ማረጋገጥ እንደተቻለው የፖሊስ ዶክትሪን ጠቅለል ያሉ መሰረታዊ አስተሳሰቦችን በማካተት ዘመናዊ የፖሊስ ተቋምን ለመገንባት የሚረዱ ፍልስፍናዎችንና እሳቤዎችን የሚይዝ ሰነድ ነው።

በፖሊስ ዶክትሪን ውስጥ የሚታዩ መነሻዎች እና ቅኝቶች ከሚያተኩሩባቸው መሰረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ የፖሊስ አገልግሎት ማህበረሰብ መር ሆኖ የማጠንጠኛው ማዕከል ደግሞ ህግን ማስከበር፣ ማህበረሰብን ማገልገልና ወንጀልን መቆጣጠር እንዲሆን ነው። በዶክትሪን ጽንሰ ሃሳብ ላይ የሚሠጡ ትርጉሞች እንደሚተረጎምበት አውድ፣ የግለሰቦች ዝንባሌና አረዳድ የተለያዩ ናቸው። ትርጉሞቹም ሁሉንም ማዕከል የማያደርጉና ለሁሉም በእኩል የማያገለግሉ ናቸው። ነገር ግን ዶክትሪን በጥቅሉ የዕዝ፣ የትምህርት እና የለውጥ መሳሪያ ነው።

ዶክትሪን ጥቅም ላይ ውሎ ማህበረሰባዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የሰውን የማሰብና የማገናዘብ ባህርይ አክብሮ ከነባራዊው ሁኔታ ወጣ ያሉ እና የላቁ አስተሳሰቦችን በማምጣት ላይ ሲሰራ ብቻ መሆኑ ላይ የጋራ መግባባት አለ። ይህም ማለት ሰውን ከሚፈለገው ውጪ እንዳያሳብ በሚያደርጉ ቀያጅ፤ የማሰብ ነጻነትን በሚያግዱ ማለትም ሰውን ኢንዶክትሪናይዝ የሚያደርጉ መዋቅራዊ እሳቤዎችን ከተቋሙ የአሰራር ስርዓት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማስወገድን የሚጠይቅ ነው።

የዶክትሪን መነሻን ለመረዳት ሲፈለግ የሚፈለገው የትርጉም ዓይነት (ለምሳሌ፡- ሀይማኖታዊ፤ ወታደራዊ ...ወዘተ) በተለይም በክፍለ ዘመናትና በተለያዩ ጊዜ ከተከሰቱ ባህሎች ጋር ሊገናኙ በሚችሉ አሻራዎች ላይ ሊያርፍ ይችላል።

የዶክትሪን መነሻ በዓለማችን በክፍለ ዘመናት ውስጥ ከተከሰቱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኩነቶች ጋር የሚሄድ ቢሆንም ስረ መሰረቱ ግን የመቄዶንያና የሮማ ወታደሮችን ጽንሰ ሀሳባዊ አረዳድ በማጣቀስ ላይ ያተኩራል። የፖሊስ የአገልግሎት ፍልስፍና በወንጀል መከላከል፤ በምርመራ እንዲሁም በፖሊስና ማህበረሰብ ግንኙነት ላይ የስራ አቅጣጫዎችን ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን ለሌሎች ደንቦችና የአሰራር መርሆዎች መነሻም ነው።

በሌላ አገላለጽ ፍልስፍና ወይም ዶክትሪን የአንድ ማህበረሰብ ወይም ተቋም የባህል እና አሰራር መገለጫም ነው። ዶክትሪን የሶስት ጉዳዮች መሰረታዊ መነሻ ሆኖም ያገለግላል። እነሱም ዶክትሪን እንደ ትምህርት፣ የዕዝ ተዋረድና የለውጥ መሳሪያነት መነሻ የሚሆንባቸው ሲሆን እርስበርስም

ተመጋጋቢዎች ናቸው። ዶክትሪን እንደ የዕዝ ተዋረድ መሳሪያነቱ ምን ማድረግ እንደሚገባ ይናገራል፡ ፡ እንደ የለውጥ መሳሪያነቱ ምን እንደምንሆን የሚገልጽ ሲሆን እንደ የትምህርት መሳሪያነቱ ደግሞ ምን እንደምናደርግና ማንነታችንን ያሳያል።

ዶክትሪን የመርሆዎችና የስታንዳርድ ኦፕሬሽን ፕሮስጄሮች ድምር ሲሆን በተለይም የቢሮ አስተዳደር ማለትም የአንድን ሀገር ፖሊስ አገልግሎትንና ሌሎች የሲቪል ተቋማትን በአጠቃላይ የሚመራ ነው፡ ፡ ዶክትሪን በአጠቃላይ በተቋማት የበላይ ሀላፊዎች፣ የፖለቲካ አመራሮች እና በሀገሪቱ ህዝብ ይወሰናል። ስለዚህ በዶክትሪኑ ውስጥ የተጠቀሱ ገዢ የአስተሳሰብ ምሰሶዎች ለፖሊሳዊ ጉዳዮች መነሻና ለድርድር የማይቀርቡ ናቸው።

በዚህ መነሻ የኢትዮጵያ ፖሊስ በራሱ ፍልስፍናና የጋራ እሴቶች የሚመራ እንዲሆን ለማድረግ ቅኝቱን የሚዘውር ዶክትሪን ማውጣት ከምንም በላይ ቀዳሚ የሆነ ስራ መሆን እንዳለበት ስምምነት ላይ ተደርሷል። ይህ እሳቤ የሌሎች ሀገራትን ልምድ የሚጋራ ሲሆን የዶክትሪኑ መኖር በዓላማው ላይ ከተጠቀሱት አንጻራዊ ጥቅሞች በተጨማሪ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ለማጎናጸፍና ለአሰራር ጥራት ዋስትና እንዲሆን ያደርጋል።

## 2.2 በፖሊስ ዶክትሪን የአገራት ልምዶች

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን አስፈላጊነት ከፖሊስ ሪፎርም አንዱ እንዲሆን ሲደረግ ታሪካዊ ዕድምታው በሀገራችን የፖሊስ ታሪክ ፊር ቀዳጅና የመጀመሪያው ያደርገዋል ። ከቃሉ ጀምሮ ያሉ አረደዶችንና የተዛቡ ግንዛቤዎችን ለማስተካከልና በዶክትሪን መኖር አስፈላጊነት ላይ አንጻራዊ ልምዶችን ጠቅለል ባለ መልኩ ማሳየት የሰነዱን ይዘት ያሳድገዋል በሚል አጠቃላይ እድምታ ይህ ርዕስ እንዲኖር ምክንያት ሆኗል ።

በበርካታ የዓለማችን አገራት የፖሊስ ዶክትሪን በፖሊስ አሰራር ላይ የሚነሱ ፍልስፍናዊ ጥያቄዎችን በመመለስ ረገድ እንደ ማገናዘቢያ ሰነድ ሆኖ ማገልገል ከጀመረ ዘመናት ተቆጥረዋል። በዓለማችን ውስጥ የታዩ የፖለቲካ አስተሳሰቦችና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስሮች በሰው ልጅ አጠቃላይ የህይወት ጉዞና በተለይም የአካባቢን ሰላምና ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ በሚቋቋሙ ተቋማት ቅርጽ፣የአሰራር ዶክትሪንና የህግ ማስከበር ተግባራት ላይ አዎንታዊም አሉታዊም ተጽዕኖ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በፖሊስ ዶክትሪን አስፈላጊነት ላይ ግን ተመሳሳይ የሆነ ግንዛቤ አላቸው።

ሀገራት በሚከተሉት አሀዳዊ ወይም ፌደራላዊ የመንግስት አወቃቀር ልክ የፖሊስ ሀይልን ያደራጃሉ። እንደመንግስታዊ አወቃቀራቸው በዶክትሪናቸው ውስጥም የአገልግሎት አሰጣጣቸው ማእከላዊነትን (Centralization) የሚያበረታታ ወይም ባልተማከለ (Decentralization) የፖሊስ አሰራር የተቃኘ እንዲሆን ያደርጋሉ። አንዳንዶች ከላይ ወደ ታች (Top-Bottom

Approach) በሚፈስ የዕዝ ተዋረድ ላይ በመመስረት የመንግስት ባለቤትነት ገዝፎ የሚወጣበት ሁኔታ ሲያደራጁት ሌሎች ደግሞ ከታች ወደ ላይ (Bottom-Up Approach) በሚሄድ አደረጃጀት የህዝብ ባለቤትነት ለየት ብሎ በሚታይበት ሁኔታ ያደራጃሉ።

አንዳንድ ሀገራት የፖሊስ ዶክትሪኖቻቸውን በፖሊስ ዋናዋና ስራዎች ላይ አተኩረው በተናጠል ያወጣሉ። ለምሳሌ፡- የወንጀል መከላከል፣ የወንጀል ምርመራ እና የፖሊስ ስነ-ምግባር ዶክትሪኖች ይሏቸዋል። በእነዚህ ዶክትሪኖች ውስጥ የሚካተቱ ርዕሶች ጠቅለል ያሉ ሲሆኑ ለድርድር የማይቀርቡ ሀገራዊ ስምምነት ያላቸው አስተሳሰቦች ናቸው።

እነዚህ አስተሳሰቦች ለፖሊስ ትምህርትና ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም ለፖሊስና ማህበረሰብ ግንኙነት መነሻ ማጣቀሻዎች ሆነው ያገለግላሉ። በዓለም ላይ ያለው ልምድ የሚያሳየው አንድ ወጥ ሆኖ የተሰነደ የፖሊስ ዶክትሪን አለመኖርን ነው። ነገር ግን በዶክትሪን አስፈላጊነትና አንኳርና ገዢ እንዲሁም ዘመን ተሻጋሪ ሀሳቦችን በመያዙ ላይ ልዩነት የለም። የዶክትሪን መኖር የፖሊስ ፕሮፌሽናሊዝምን ለማሳደግና ከሌሎች ተጽዕኖዎች ለመከላከል የሚጠቅም መሆኑ ዓለምአቀፍ እውነታና ስምምነት ያገኘ አስተሳሰብ ነው ።

የፖሊስ ዶክትሪንን ማዘጋጀት ሀገራት በተቋሙና በአገልግሎቱ ላይ ተቀራራቢ አስተሳሰብ ደረጃ ላይ እንዲደርሱና ከጊዜ ለውጥ ጋር አብሮ የሚሄድ የፖሊስ ተቋም ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡ ፡ በአሰራራቸውና አገልግሎታቸውም የህዝብ ተቀባይነትን ማትረፍ እንዲችሉ ከማድረጉም በላይ ተቋማዊ ብቃትንና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠትም ረድቷቸዋል።

በተለያዩ የፖለቲካ ውዥንብሮች እና የመንግስታት ለውጦች አንዴ እየፈረሰ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደአዲስ እየተገነባ የሚሄድ ተቋም እንዳይሆንም ከማድረጉም በላይ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትንም አስተማማኝ አድርጎታል። ከእነዚህ ልምዶች በመነሳት የፖሊስ ዶክትሪን መኖር ወሳኝና ለፖሊስ ተቋም ዋስትናን የሚያረጋግጥ መሆኑን መረዳት ይቻላል ።

# ክፍል ሶስት

## የኢፌዲሪ ፖሊስ ዶክትሪን መሰረታዊ ምልከታዎች እና እሴቶች

### 3.1. የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን መነሻ ሃሳቦች እና ምልከታዎች

የኢፌዲሪ ፖሊስ ዶክትሪን መነሻ ሀሳቦች ወይም ፍልስፍናዎች አንዱ ፖሊስን ወታደራዊ ያልሆነ (Demiliterized) ፣ የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለው (Depoliticized) ፣ አገልግሎቱ ያልተማከለ (Decentralized) እና ዲሞክራሲያዊ (Democratized) እንዲሆን ማድረግ ነው።

የፖሊስን ተቋም ኢ-ወታደራዊ (Demiliterized) የማድረግ አጀንዳ እንደ መንግስታት የአስተዳደር ሁኔታ የሚወሰን ቢሆንም ከፖሊስ አጠቃላይ የስራ ባህርያትና አስተዳደር አኳያ ሙያው በዲሲፕሊንና በእውቀት የተደራጀ እንዲሆን ስር በሰደዱ ወታደራዊ መሰል የፖሊስ ባህሎች ላይ ተጽዕኖ በማደረግ የባህል ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ዶክትሪን ኢ-ወታደራዊ የሆነ የፖሊስ ተቋምን መገንባት ማለት ተቋማዊ አስተሳሰቡ፣ አሰራሩ፤ ትጥቁ እና በአባላት የህግ ማስከበር ስራ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች በፖሊሳዊ ቅኝት የተቀመሩ ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ወንጀልን በመከላከልና ስርአትን በማስፈን ረገድ የሚኖረውን የፖሊስ የአካል ብቃትና ስነልቦናዊ ዝግጅትን አይጨምርም፡፡

በወንጀል መከላከል ስርዓት ውስጥ ህገ ወጥ ሰልፎችን የመበተን፤ በከተማም ሆነ በገጠር የሚኖረውን ማህበረሰብ ሰላምን የሚያውኩ ሽፍቶችንና ጸረ ሰላም ሀይሎችን በሀይል ለመደምሰስ ታጋቾችን ለማስለቀቅ፤ ስርዓትን ለማስፈንና የተደራጁ ወንጀለችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ ፖሊሳዊ ዝግጅቶችንና ከፊል ወታደራዊ (Para-militery) የሆኑ ባህሎቹን የበለጠ እንዲጠናከሩ የሚደረግበት ነው፡፡ የፖሊስ ታክቲካል ብቃትና ምላሽም በነዚህ ሁሉ እይታዎች የሚቀመር ስትራቴጂ ይሆናል ፡፡

የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለው (Depoliticized) የፖሊስ ተቋም ማለት ለማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የማይወግን ሆኖ ለህዝብና ለሀገር ሰላምና ደህንነት የሚሰራ ተቋም ማለት ነው፡ ፡ በሌላ አገላለጽ የፖሊስ ተቋማዊ ነጻነትን በማረጋገጥ የሌሎች አካላትን ጣልቃ ገብነት መከላከል ማለት ነው፡፡ በዚህ መነሻም በሀገራችን የፖለቲካ ተቋምና ስርዓት ውስጥ ፖሊስ በማንኛውም መንገድ የፖለቲካ መሳሪያ አይደለም የሚለው ስምምነት ማግኘት ይገባዋል ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፖሊስ በህዝብ ይሁንታ ላገኘ መንግስት ብቻ ይሰራል፡፡

በአገልግሎት አሰጣጡ ያልተማከለ (Decentralized) ማለት በሀገሪቱ ህገ መንግስትና በፖሊስ የማቋቋሚያ አዋጆች የተደነገጉ የፖሊስ ስልጣኖችንና ኃላፊነቶችን እስከ ታችኛው የፖሊስ አወቃቀር በማውረድ አገልግሎቱ በሚሰጥበት ቀዬ አጠቃላይ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ላይ ወስኖ ለመስራት የሚያስችል ኃላፊነትንና ስልጣንን መስጠት ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩልም በዚህ ዶክትሪን አሳታፊነት ማለት በፖሊስና ማህበረሰብ መካከል በሚደረግ ግንኙነት የማህበረሰብንና ሌሎች ድርሻ ያላቸውን አካላት በወሳኝነት በየደረጃው በማሳተፍ መልካም ግንኙነትን ማሳደግ ማለት ነው ፡፡

ሁለተኛው የዶክትሪኑ አስተሳሰብ ወይም ምልከታ መነሻ የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግን አጠቃላይ ፍልስፍና ወይም አስተሳሰብ የእሳቤው ማዕከል በማድረግ፤ ችግርን በመፍታትና አጋርነትን በማጠናከር ህዝብንና የህዝብን ንብረቶች ከመጠበቅ፣ ህግን ከማስከበር፣ ወንጀልን ከመከላከልና ከመቆጣጠር በላይ በማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ላይ መሰረታዊ ለውጥ እስከማምጣት የሚሰራ ተቋም በማድረግ ከዘመናችን ሚዛን ደፊ የፖሊስ ስትራቴጂዎች አንዱን የማሳካት እሳቤ ነው፡፡

በዚህ ዶክትሪን በማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ለውጥ ማምጣት ማለት አጉል የሆኑና በማህበረሰብ የማይደገፉ ባህርያትን በማስወገድ መልካም ባህሪይንና አመለካከትን በማስረጽ በህዝቦች መካከል አብሮ የመኖር ባህልን ማዳበር እና የላቀ የሞራል ልዕልናን መገንባት ማለት ነው። በተጨማሪም በማህበረሰብ መካከል መልካም እሴቶች ላይ የተገነባ ጠንካራ ማህበረሰባዊ ትስስር እንዲገነባ ማድረግም ነው።

ሶስተኛው የኢትዮጵያ ፖሊስ ፍልስፍና መነሻ አስተሳሰብ የፖሊስ አገልግሎት በዲሞክራቲክ ፖሊሲንግና የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ፍልስፍናዎች በተቀመረ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ዴሞክራቲክ ፖሊሲንግ ሲባል የፖሊስ አባላትና የፖሊስ ተቋም በሀገሪቱ ፖሊቲካ ውስጥ ተሳትፎ ይኖራቸዋል ማለት አይደለም።

በአገልግሎት አሰጣጡ ዲሞክራሲያዊ (Democratized) ነው ማለት አስተሳሰቡና ቅኝቱ በዲሞክራሲያዊ እሴቶች እና መርሆዎች ላይ የተገነባ ነው ማለት ነው። ይህም ማለት የፖሊስ ተቋም ህዝብ መር፤ አሰራሩ ግልጽ በፖሊስና ህዝብ ግንኙነቶች ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን የጠበቀ ማለት ነው። የፖሊስንና የማህበረሰብ ግንኙነትን በዲሞክራሲያዊ አግባብ እንዲሆን በማድረግ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ማቅረቢያ ስርአቶችንና የስራ አፈጻጸምና አገልግሎት የሚቆጣጠሩ ገለልተኛ ቦርዶችንና ግሩፖችን ያደራጃል።

ከዚህ በተጨማሪ ፖሊስ በማንኛውም የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ምንም ዓይነት የጣልቃ ገብነት ሚና አይኖረውም ማለትም ነው። የዚህ አስተሳሰብ ማዕከሉ የፖሊስ ተቋማት በህግ በተሰጣቸው የስልጣን ገደብ ውስጥ በመወሰን አገልግሎታቸው ከምንም ነገር ነጻና ከአድሎአዊነት የጸዱ የፍትህ ተቋማት አካሉ ይሆናሉ የሚለው ነው።

ነገር ግን ዲሞክራቲክ ፖሊሲንግ ማለት የፖሊስ አባላት የፖለቲካ መብት የላቸውም ማለት አይደለም። ፡ የፖሊስ አባላት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ድምጻቸውን ለሚፈልጉት የፖለቲካ ድርጅት የመሰጠት፣ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብታቸውን ጨምሮ ሰብአዊ መብታቸው የተከበረ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር በሚካሄዱ ማንኛቸውም ዓይነት እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ ሙሉ መብት አላቸው።

ይህ አስተሳሰብ በዋናነት የፖሊስ አባላት በፖሊስ ትምህርትና ስልጠና በሚያገኙት ዕውቀት፣ ክህሎትና የሙያ ፍቅር ለሙያቸው ከፍተኛ ግምት በመስጠት (Professional Standards) ሙያቸውን ከግል ፖለቲካዊ አለመካከታቸው ለይተው በመረዳት ታማኝና ለሙያውም ቀናኢ ይሆናሉ የሚል ነው።

የዲሞክራቲክ ፖሊሲንግ ፍልስፍና የፖሊስ አባላት በዲሞክራሲያዊ አግባብ ይመረጣሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን ፖሊስ የሚያገለግለው በዲሞክራሲያዊ ምርጫ የተመረጠን መንግስት ሲሆን ከዴሞክራሲያዊ እና ህጋዊ ምርጫ ውጪ ወደ ስልጣን የመጣን መንግስት አይቀበልም። ይልቁንም

ወደ ስልጣን የመጣበት መንገድ ህገወጥ ከሆነ በምርመራ በማጣራት በህግ እንዲጠየቅም ያደረጋል፡ ፡ ከህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ውጭ በመፈንቅለ መንግስትና ሌሎች አማራጮች ወደ ስልጣን የመጡ ግለሰቦችን፤ ቡድኖችን፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ይገዳደራል በቁጥጥር ስር አድርጎም ያጣራል። ከዚህ በተቃራኒ ወደ ስልጣን የመጣው መንግሰት የመጣበት መንገድ ህገ-መንግስታዊና ተአማኒነቱ ተቀባይነት ያለው ከሆን በመንግሰት ላይ የሚወሰዱ ጥቃቶችን ይከላከላል።

በሌላ በኩልም በዲሞክራቲክ ፖሊሲንግ አስተሳሰብ መንግስት ከህግ አግባብ ውጪ ፖሊሲን በቀጥታ አያዘውም ማለት ነው። የዚህ አስተሳሰብ መነሻ ፖሊስ በፖሊሳዊ ሳይንስና ዕውቀት የሚመራ ነው የሚል ነው። በህገ መንግስታዊ ሥርዓቱ መሰረት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ወደ ስልጣን የመጣ መንግስት በህዝብ ተቀባይነት ስለሚኖረው ፖሊስን በማስተዳደርና አፈጻጸሙንም በመቆጣጠር ረገድ ህጋዊ ስልጣን ይኖረዋል።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ህዝብ ስሜቱን ያለምንም ፍርሀትና ስጋት የሚገልጽበት ወይም ከማጠናከር አንጻር የፖሊስን እና የህዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚረዳ የግንኙነት መስመር እንዴት ማስመር ይቻላል የሚል ነው። ይህን የብዙዎች ጥያቄ ሊፈታ የሚችለው "በዲሞክራሲያዊ ምርጫ አብላጫ ድምጽ አግኝቶ የተመረጠ መንግስት የህዝብ ውክልና አለው" የሚለው ሲሆን ህዝብ በፖሊስ ላይ የሚሰማውን ስሜት ለማንጸባረቅ የሚችልበት አንዱ መንገድ ደግሞ "ህዝብ የመረጥኩት መንግስት አለኝ" ማለቱ ነው። ይህም ማለት የፖሊስን አገልግሎት በበላይነት የሚመራውም ሆነ የሚቆጣጠረው ይህው በህዝብ የተመረጠው መንግስት ስለሚሆን በተዘዋዋሪ/በተወካዮቹም ቢሆን ህዝብ ፖሊስን የመቆጣጠር ዕድል አለው ።

ስለዚህ የኢፌዲሪ ፖሊስ ዶክትሪን በዲሞክራቲክ ፖሊሲንግና ኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ፍልስፍናዊ ዳይሜንሽኖች ላይ መሰረቱን በማኖር ህዝብን ማዕከል ባደረገ ስራ ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን በመቀነስ እንዲሁም የማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ ላይ ለውጥ በማምጣት ፖሊስን እና ማህበረሰብን ወደ አንድ ላቅ ያለ ደረጃ በማሸጋገር ላይ የሚሰራ ነው። በሀገራችን የፖሊስ ስትራቴጂ ኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ በማህበረሰብና ፖሊስ መካከል በሚፈጠር መልካም ግንኙነት የአካባቢውን ችግር በጋራ መለየትን ለችግሩ መፍቻ ሀሳቦችን ማመንጨትንና መተግበርን ያካትታል። የችግር አፈታት ዘዴው ሀገር በቀል ዕውቀቶችንና በቀዬው አጠቃላይ አውድ ውስጥ የሚታዩ ባህላዊ፤ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባ መሆን ይገባዋል ።

ኮምዩነቲ ፖሊሲንግ የመንግስትን፤ የፖሊስ ተቋማትን፤ የማህበረሰቡንና፤ የፖሊስ አባላትና ጽኑ ፍላጎት ይጠይቃል። ኮምዩነቲ ፖሊሲንግ ባልተማከለ የስልጣን ክፍፍል የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰሮችን በማብቃት የቀጠናቸው ወሳኝ ኃላፊዎች እንዲሆኑ ማድረግን ይጠይቃል ።

ይህም በሙሉ ነጻነትና የኃላፊነት ስሜት የአካባቢውን ችግር በአካባቢው (ከተማም ሆነ ገጠር) አጠቃላይ ማህበራዊ ፤ ስነ ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ አውድ ላይ በመመሰረት መፍታትንና አካባቢውን ከወንጀልና የወንጀል ስጋት ነጻና ሰላማዊ ማድረግን ይፈልጋል። ስለዚህ ኮምዩነቲ ፖሊሲንግ በፖሊስ

ተቋማዊ እሴቶች ላይ በማተኮር የማህበረሰቡን ተሳትፎ ማጎልበትና ቁልፍ ከሆኑ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ውስጥ ያልተማከለ አደረጃጀትን በማበረታታት በችግር አፈታት ዘዴ ችግሮችን መለየትና መፍታትን ይፈልጋል ።

ለኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ስኬት ሲባል የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ ማበልጸጊያ ተቋማት በብዛት ይከፈታሉ፡፡ በማበልጸጊያ ተቋማቱ የማህበረሰብ ደህንነት ፓትሮል(ቅኝት)(Neighbourhood Watch Program) ፕሮግራም እንዲለመድ ይደረጋል ። ነጻና ገለልተኛ የሆነ የአማካሪ ቡድን ከታች እስከ ላይ ድረስ ይደረጃል ።

አራተኛው የዶክትሪኑ መነሻ አስተሳሰብ የፖሊስ አገልግሎት ብቃት የሚለካው በህዝብ እርካታ ብቻ ነው የሚለው ነው። የህዝብን እርካታ ለመለካት የሚረዱ ተብለው የሚገመቱ መለኪያዎች እና የመለኪያዎቹም የመለካት አቅም ተሞክሮ ማረጋገጫ ያላቸው መለኪያዎች ሊዘጋጁ ይገባል።

በአጠቃላይ ለፍልስፍናው ስኬት ዋናው መሰረትም የፖሊሳዊ ዕውቀት ማረጋገጫ ሲሆን የሚገኘውም በህግ እውቅና ከተሰጣቸው የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ነው። በነዚህ ተቋማት ውስጥ አልፎ ማረጋገጫ የሌለው አባል በሀገሪቱ ፖሊስ ስርዓት ውስጥ በፖሊስ ኃላፊነትና አባልነት ማገልገል አይችልም። ይህ ደግሞ በፖሊስ ተቋም ውስጥ ለድርድር የማይቀርብ ገዥው የፍልስፍናው ማዕከላዊ ሀሳብ ነው።

ሌላው የኢትዮጵያ ፖሊስ ዶክትሪን መነሻ ሃሳብ በፖሊስ እሴትነት የተለዩና በብቃት ረገድ ዋና የሚባሉ የብቃት ማረጋገጫ መርሆች የአስተሳሰቡ መሰረቶች መሆናቸው ነው። እነዚህ የፖሊስ እሴቶችና መርሆዎች የፖሊስ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መነሻ ናቸው።

የኢፌዴሪ ፖሊስ ዶክትሪን መቋጫም በትምህርትና ስልጠና ውስጥ የተጠቀሱ ዋና ዋና ሀሳቦች፣የፖሊስና ማህበረሰብ ግንኙነት መሰረቶችና በኮምዮኒቲና ዲሞክራቲክ ፖሊሲንግ ፍልስፍናዎች ውስጥ የተቀመጡ አንኳር ነጥቦች ብቻ ናቸው። የማጠንጠኛው ቁልፍ ነጥቦችም ፖሊስ ከፖሊቲካ ነጻ፣ በተቋማዊ ቅርጹ ኢ-ወታደራዊ፤ በአሰራሩና አደረጃጀቱም ያልተማከለና አሳታፊ ሆኖ በስልጣን ክፍፍል ከህዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የፖሊስ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በተሰጣቸው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት ወስነው እንዲሰሩ የሚያበረታታ ይሆናል።

## 3.2. የኢትዮጵያ ፖሊስ የሚመሰረትባቸው እሴቶች

እሴቶች የአንድ ተቋም መሰረታዊ እምነቶች እና መርሆዎች ናቸው። የአንድን ተቋም ውስጣዊ ባህርይ፣ ከማህበረሰቡ፣ ከሌሎች ተቋማት እና ከቀሪው ዓለም ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በተመለከተም አቅጣጫን የሚያመለክቱ እና የሚወስኑ አስተሳሰቦች ናቸው። እሴቶች በተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ተቋሙ ላስቀመጣቸው መሰረታዊ ግቦች ስኬት በባህሪያቸውና በአመለካከታቸው ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ መሪ መርሆዎችም ናቸው።

እሴቶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ሲሆን በተለይም ዋና ዋናዎቹም፣ የተቋማቱን ባህሪ ይወስናሉ፡ ፡ መልካም ተቋማዊ ባህል እንዲገነባም መሰረት ይጥላሉ። በተቋሙም የግለሰቦችን የስራ ፈጠራና ተነሳሽነት፣ ተሳታፊነት፣ ባለቤትነት እና ግንኙነትን ያጠናክራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የተቋሙ ሰራተኞች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግንኙነቶቻቸውን በመልካም የመሰረት ድንጋይ ላይ እንዲያኖሩ ይረዳሉ።

የፖሊስ እሴቶች የፖሊስ አባላትን ከፖሊሳዊ ሙያቸው በተጓዳኝ ተገቢ የሆነ የሞራልና የስብዕና ብቃታቸውን ከመገንባት በተጨማሪ የተቋሙን ህልውና የሚወስኑ ገዢ እምነቶችም ናቸው። ከፖሊስ ተቋሙ አገልግሎት ተቋዳሽ የሆነውን ህዝብ ከተቋሙ መሰረታዊ እምነቶች ጋር በማስተዋወቅ በመርህ ላይ የተመሰረተ ትብብር፣ እገዛ እና አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

የነዚህ ድምር ውጤት መጨረሻም የላቀ እና ደረጃውን የጠበቀ ፖሊሳዊ አገልግሎት እንዲሰጥ በማስቻል ከፍተኛ ስኬት እንዲያስመዘግብ ያደርገዋል። በጽኑ መሰረት ላይ የተገነቡ እሴቶች ፖሊስን በተቋማዊ ብቃቱ ከሌሎች የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተመራጭና ሳቢ እንዲሆን ያደርገዋል።

የኢፌዲሪ ፖሊስ ተቋም ከላይ የተጠቀሱትን ዘርፈ ብዙ ውጤቶች እንዲያገኝ የሚያስችሉት አራት እሴቶች ከዚህ በታች ተቀምጠዋል። የእነዚህ የእሴቶች ዋነኛ መሰረትም የተቋሙ ተልዕኮና ራዕይ ናቸው። ሲደራጁም ለየት ያለ ይዘት እንዲኖራቸው የተደረገ ሲሆን በቀላሉ ለማስታወስና ለመረዳትም ምቹ ሆነው ተቀምረዋል። እሴቶቹም ከነዝርዝር ማብራሪያቸው ከዚህ በታች ቀርበዋል።

## 3.2.1. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)

የሙያዊ ብቃት እሴት ማለት ከመሰረታዊ የፖሊስ ሙያ ስልጠና ጀምሮ በተለያዩ የማዕረግና መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ውስጥ የሚገኙ የፖሊስ አባላት የማህበረሰብን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ ከወንጀልና የወንጀል ስጋት ነጻ የሆነ አካባቢን በመፍጠር የተሰጣቸውን የህዝብ አደራ ለመወጣት የሚያስችላቸው የላቀ የእውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ደረጃን የማሟላት እሴት ማለት ነው።

የሙያዊብቃትእሴትበውስጡ፣ፖሊሳዊሙያዊብቃት (PoliceProfessionalism) ፣ የላቀ የፖሊስ አገልግሎት (Service Excellence) ፣ የስራ ባልደረባን፣ አጋሮችን፣ የባለድርሻ አካላትን እና የህዝብን የላቀ ተሳታፊነትን የመጠቀምና የማሳደግ ጥበብን (Participatory and Partnership) የያዘ ነው። በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት (Transparency and Accountability) ፣ተፅዕኖንና ጣልቃ ገብነትን ያለመቀበል፣ በነፃነት የመስራትብቃት (Independency) ፣የሚሉትን መሰረታዊ መርሆዎች በእለት ተእለት የፖሊስ ስራ ውስጥ በማካተት ፖሊሳዊ ተግባርን ማከናወንን የሚጠይቅ እና የሚያቅፍ ፖሊሳዊ ብቃት እሴት ነው።

በፖሊስ ተቋም ውስጥ የፖሊሳዊ ሙያን በማሳደግ በአገልግልት አሰጣጡ ምጡቅ፣ ተአማኒና ቀጣይ የሆነ ኢትዮጵያዊ የፖሊስ ተቋም መገንባት ቸል ሊባል የማይችል መሆኑን ማመንና ለዚሁም ሁሉንም ምቹ ሁኔታዎች እና አጋጣሚዎች በተገቢው መንገድ መጠቀም እንደሚገባ መቀበል ያስፈልጋል፡ ፡ ከዚህ አንፃር የሚከተሉት እምነቶች እና እሳቤዎች የዚህ እሴት ዋና ዋና መገለጫዎች ናቸው። እነሱም በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ሙያዊ ብቃትን ማሳየት እና ማስመስከር፣ ከግላዊ ፍላጎት ይልቅ በሙያዊ ብቃት ላይ መመስረት፣ብኩንነት እና አላስፈላጊ ኪሳራን ማስወገድ፣ጊዜን እና ግብአትን በተገቢው መጠቀም ፤ ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ ቴክኖሎጂዎችን በማበልጸግ ስራ ላይ ማዋልና ለውጥን መቀበል ናቸው።

በተጨማሪም በስራ አፈፃፀም ላይ የሚታዩ ግድፈቶችን በወቅቱ ማረም እና ገንቢ ሃሳብ መስጠት፣ ለስራ አፈፃፀም ብቃት እና ለጠቅላላ ስኬት የራስ (የግል) ጥረትና ሚና እጅግ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን ማመን እንዲሁም ማህበረሰቡ በፖሊስ ላይ ያለው እምነት እንዲዳብር፣ የአገሪቱን ህጎች በመቀበልና በመጠበቅ እንዲሁም የግል እውቀትንና ተሞክሮን በማሳደግ፣ ለፖሊስ ሙያ መበልጸግ ያልተቆጠበ አስተዋፅኦ ማድረግም በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

በሌላ በኩልም ለሰራተኞች (ለአባላት) ስልጣንና ሀላፊነት በመስጠት የላቀ የፖሊስ አገልግሎትን ወደሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ፣ በማንኛውም የተቋሙ ጉዳዮች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ብቃታቸውን ማሳደግ እንዲሁም ምን እንደሚጠበቅባቸው፣ እንዴት እንደሚመዘኑና ስኬታቸውም እንዴት እንደሚለካ ወይም እንደሚመዘን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ እሴቱ ከሚይዛቸው እሳቤዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 3.2.2. ምሉዕነት/ታማኝነት (Integrity)

በፖሊስ ተግባር ውስጥ ታማኝነት ወሳኝ ከሆኑ እሴቶች ውስጥ አንደኛው ነው። ታማኝነት የላቀ የሞራል ብቃት፣ ሃቀኝነት፣ ቅንነት እና የአገልጋይነት መንፈስን በመላበስ ፖሊሳዊ ተግባርን የማከናወን የፀና እምነት መያዝ ማለት ነው።

የታማኝነት እሴት ተቋሙም ሆነ የፖሊስ አባላት ለማህበረሰቡ፣ ለሀገር፣ ለህግ እና ለራሱ ታማኝ የመሆን፣ ቀና እምነትን የመያዝ እሳቤዎችን አጠቃሎ የሚይዝ ሰብአዊ እና ፖሊሳዊ የብቃት ማሳያ እሴት ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተሉት እምነቶች እና እሳቤዎች የዚህ እሴት ዋና ዋና መገለጫዎቹ ናቸው። እነሱም፣

ሁልጊዜም ለራስ፣ ለስራ ባልደረቦች፣ ለህዝብ፣ ለሀገር እና ለህግ ታማኝ መሆን፣ ስልጣንና ሃላፊነትን ተገቢ ላልሆነ ተግባር አለማዋል፣ ከራስ ጥቅም ይልቅ የህዝብን ጥቅም በማስቀደም ተልዕኮን መፈፀም እንዲሁም የመንግስትን ንብረት፣ ለስራ ማከናወኛ የተመደበ በጀትን እና ሌሎችን በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝና ማስተዳደር ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ፖሊሳዊ ተግባርን በፍትሃዊነት፣ ያለአድልዎ እና በታማኝነት መፈፀም፣ ፖሊሳዊ ስራዎቹን ሲያከናውንና ለህዝብ የድረሱልኝ ጥሪዎች ምላሽ ሲሰጥ ምንም ዓይነት ክፍያ አለመጠበቅ፣ አለመጠየቅና አለመቀበልን ይጨምራል።

ከማንኛውም ሰው ጋር በቅንነት እና በሃቀኝነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ማድረግ፣ ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት ራስን ማግለል እና ከማንኛውም አቅጣጫ የሚመጡ ተፅዕኖዎችን በፅናት መገዳደር እና ህዝብን ለማገልገልና የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት አካላዊና ሞራላዊ ዝግጅቱን ለማሳደግ ብቃቱን ማሳደግና አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን እሴቱ ከሚይዛቸው እሳቤዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

## 3.2.3. ብዛህነትን ማክበር (አካታችነት) (Respect for Diversity)

ብዝሃነትን የማክበር እሴት ማለት ለተለያዩ የዘር፣ የብሔር፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የዕድሜ፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያ ደረጃ፣ የአካላዊና አእምሯዊ ብቃት፣ የአምልኮ/እምነት፣ የፖለቲካ አቋምና እምነት፣ ወይም ለማንኛዉም አመለካከት (Ideologies) ክብርን በመስጠት እና በማክበር የማገልግል የፀና እምነት የመያዝ እሴት ማለት ነው።

ይህን መሰረት በማድረግ ብዝሀነትን የማክበር እሴት የፖሊስ አገልግሎትን በእኩልነትና ያለአድልዎ የመስጠት እና የብዙሃንን ይሁንታ ማግኘትን ለፖሊስ ስራ ውጤታማነት አጋርነትን በመልካም ግንኙነት ላይ የመገንባት እሳቤዎችን በውስጡ የያዘ እሴት ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተሉት እምነቶች እና እሳቤዎች የዚህ እሴትዋናዋና መገለጫዎቹ ናቸው። እነሱም፣

ለዜጎች እሴቶች፣ እምነት፣ ወግ፣ ባህል፣ ግላዊ ፍላጎትና፣ አመለካከት ተገቢውን ክብር መስጠት እንዲሁም በማንኛዉም ጊዜና ስፍራ በማህበረሰቡ ደስታና ሀዘን ጊዜ ተሳትፎ ማድረግ ናቸው። በተጨማሪም ማንኛውም ሰውን እና ቡድንን ካለው ስልጣን፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ አንጻር አለማየትና አገልግሎትን ያለአድሏዊነት እና ልዩነት በመስጠት “ሁሉም ሰው በፖሊስ ፊት እኩል ነው” የሚሉትን መርሆዎች ይይዛል።

እንዲሁም ወንድና ሴትን በእኩልነት ማስተናገድን እና ለሰራተኞች (ለአባላት) ተገቢውን ዋጋና ቦታ መስጠትን፣ ወደ ተቋሙ ይዘዋቸው የሚመጡትን የብዝሀነት መሰረቶች መቀበል እና ማክበርን፣እንዲሁም የፖሊስ አባላት ህዝብን ለመጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ተካፋይ መሆን ክብር እና ኩራት መሆኑን ማመን እሴቱ ከሚይዛቸው እሳቤዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 3.2.4. ሰብዓዊ መብት ማክበር (Respect for Human Rights)

ሰብዓዊ መብት የማክበር እሴት ማለት የሰው ልጅ “ሰው” በመሆኑ ብቻ የሚያገኛቸው የማይጣሱ እና የማይገፈፉ መብቶችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ ማክበር ነው።

የዜጎችን መብት አለመጣስ ፖሊሳዊ ሙያንና ፖሊስ በመሆን የተገኙ ስልጣኖችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መተግበርንም ይጨምራል፡፡

ስለሆነም ሰብዓዊ መብት የማክበር እሴት በውስጡ ማንኛዉም ፖሊስ የሰብዓዊ መብት ህጎችን በእኩልነት የማክበር፣ በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸውን ተጎጂዎች በርህራሄና በክብር ማስተናገድ፣ በወንጀል ተጠርጣሪዎችን ሰብአዊ መብቶች በማክበር ያልተገቡ አያያዞችንና የምርመራ ዘዴዎችን አለመጠቀም፣ የሀይል እርምጃ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ያለመጠቀም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተመጣጣኝ ሀይል የመጠቀም እሳቤዎችን ይጨምራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሰላማዊ ስብሰብ ወቅት እና በማንኛውም ሁኔታ የሀይል እርምጃ ያለመውሰድን ወይም ሁኔታው በራስ ላይና በሌሎች ላይ የህይወት ወይም ሌላ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ከሆነ ብቻ ተመጣጣኝ ኃይል መጠቀምን ያካትታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ያለህግ አግባብ ሰዎችን ያለመያዝና ያለማሰር፣ በፖሊስ ማረፊያ ቤት ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በህግ አግባብ ብቻ የመፈፀም እሳቤዎችን አካቶ ይይዛል ፡፡

በተጨማሪም በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች ህጋዊ መብቶቻቸውን የማክበር እና በሰብአዊነት በተገቢው ክብር የመያዝ፣ በሰዎች ላይ ማንኛውም የህግ ጥሰት ያለመፈፀም እንዲሁም ሰዎችን እና ማስረጃዎችን ያለመሰወር እና ያለማጥፋት የሚሉትን መሰረታዊ እሳቤዎችን ያቀፈ እሴትም ነው፡ ፡ ከዚህ አንፃር የሚከተሉት እምነቶች እና እሳቤዎች የዚህ እሴት ዋና ዋና መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ እነሱም፣ የፖሊስ አባላት ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው እንደሚፈልጉት ሁሉ የማህበረሰቡን እና የስራ ባልደረቦቹን ሰብአዊ መብት ሁልጊዜም ማክበር፣ የሰዎችን ነፃነት መጠበቅ፣ መብትን አለመጣስ፣ በግለሰባዊ ፍላጎት ወይም በቤተሰባዊ ህይወት ላይ ጣልቃ አለመግባትን ያካትታል፡፡

በሌላ በኩልም አላስፈላጊ ሀይል እና እርምጃ አለመጠቀም እንዲሁም ለሚወሰደው ማንኛውም ሀይል እና እርምጃ ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለ ማወቅ፣ ሰዎችን መግረፍ፤ ከወንጀል ጋር ግንኙነት የሌለውን ሰው አለማሰርና ንብረቶችን በኤግዚቪትነት አለመያዝ እንዲሁም ለማሰር መነሻ የሆኑ ማስረጃዎች ሳይሟሉ በቁጥጥር ስር አለማዋልና ክብረ-ነክ ተግባራትን አለመፈፀምን ይይዛል፡፡

በፖሊስ ተቋምና በፖሊስ አባላት የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዳይፈጸም የበኩልን ድርሻ መወጣት፣ በአጠቃላይ በህግ ጥላ ስር ያሉ ተጠርጣሪዎችን ሰብዓዊ አያያዝ ላይ ጉዳዬ ብሎ መከታተልና ክብር መስጠት ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ አስተሳሰቡ ለሰብአዊነት ቅድሚያ የሚሰጥ መሆኑን በመረዳት ፖሊሳዊ ሃላፊነትን በህዝብ የበላይነት ላይ ማኖርን ይይዛል፡፡

በተጨማሪም ማንኛዉም የፖሊስ ምርመራ ተግባር በሚከናወንበት ወቅት በህግ አግባብ እና በምርመራው ዓላማ ብቻ ላይ በመመስረት ማከናወን እንዲሁም ማንኛውንም ተጠርጣሪ ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ እንደ ጥፋተኛ አለመቁጠር እሴቱ ከሚይዛቸው እሳቤዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

# ክፍል አራት

## የኢፌዲሪ ፖሊስ የአስተሳሰብ እና የድርጊት መርሆዎች

### 4.1. የፖሊስ ተቋማት ትኩረት ህግጋት እና አደረጃጀት ዶክትሪን፣

በዚህ ክፍል ውስጥ የኢፌዲሪ ፖሊስ የሚለው ቃል የዶክትሪኑን አፈጻጸም በመላው ሀገሪቱ በሚሰጡ ማንኛውም የፖሊስ ተቋማትና አገልግሎቶች ላይ የሚሰራ የፖሊስ የጋራ መግባባት የተደረሰበት አስተሳሰብ መሆኑን የሚያሳይ ነው ። በዚህ የተነሳም የዚህ ዶክትሪን ድጋፍ የሌለው ወይም መነሻው ይሄ ዶክትሪን ያልሆነ የፖሊስ ስልጠና፣ ትምህርት፣ ኦፕሬሽን፣ ጥናትና ምርምር፣ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ወዘተ...ተግባራዊ አይሆኑም ። መነሻውም ደረጃውንና አገራዊ ስታንዳርድን የጠበቀ አገልግሎት በሁሉም የመስተዳደር አወቃቀር እንዲኖር ማድረግ ነው።

### 4.1.1. የኢፌዲሪ ፖሊስ አሰራርን የሚወስኑ ህጎች እና ደንቦች፣

ፖሊስ የታጠቀና ህግን ለማስከበር የሀይል እርምጃ እስከመውሰድ የሚደርስ በህግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ነው። በሌላ በኩል ፖሊስ ለዲሞክራሲ ስርዓት ስርጸት በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አንዱና ዋነኛው ሲሆን የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች አክብሮ እንዲያስከብር በህግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም መሆኑ ደግሞ ከሌሎች ጎላ ብሎ እንዲታይ የሚያደርገው ባህሪይ ነው።

በመሆኑም የኢፌዲሪ ፖሊስ ተልዕኮ መሰረታዊ መነሻ ከህዝብ ፍላጎት የሚመነጩ እሳቤዎች ሲሆኑ የፖሊስን አገልግሎት ውጤታማ ለማድረግ፣ የህዝብን ፍላጎት በማሳካት ተቀባይነትን ለማትረፍ በባህርያቸው ለየት ያሉ እሴቶችን ይዞ የሚገነባም የህዝብ ተቋም ነው።እነዚህ እሴቶችም ለተልዕኮው መነሻዎች ሲሆኑ ለድርድር የማይቀርቡ፣ ጊዜና ሁኔታ የማይለውጣቸው ተቋማዊ እሴቶቹ ናቸው።

በዚህ ዶክትሪን ላይ የተቀመጡ ጠቅለል ያሉ የአሰራርና የህግ ማስከበር ተግባሮች በመጨረሻ ለተለያዩ ህጎች፤ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች መነሻዎች ናቸው። እነዚህም ፖሊስ ስራውን በገለልተኝነትና በታማኝነት እንዲፈፅምና ህዝብ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ ህግንና ስርዓትን የማስከበር ግዴታና ሃላፊነትን ያለምንም ቅደም ሁኔታ የሚሰጡ ናቸው። በፌዴራልም ሆነ በክልል ፖሊስ ተቋማት ደረጃ የሚዋቀረው ፖሊስ የመጨረሻ ግቡ የኢትዮጵያን እና የህዝቦቿን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ ነው።

የፖሊስ የህግና የአሰራር ዶክትሪን መኖር ወጥነትን ለማረጋገጥ ፤ በመርህ የሚመራና ከህዝብ በመነጨ ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት የሚሰራ የህዝብ ተቋም እንዲገነባ ያደርጋል። የፖሊስ ተቋምን ብቃትና አገልግሎት አሰጣጥ ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ዕውቀቶችን፤ የፖሊስ ቴክኖሎጂዎችንና ቁሶችን በማሟላት ረገድ ከህዝብና መንግስት የሚመደቡ መዋእለ ንዋዮች እንዲሁም ይህንን ዶክትሪን

ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ህጎችና አሰራሮች መኖራቸውን ህዝብና መንግስት እንዲያረጋግጡ እድልም የሚሰጥ ነው።

የፖሊስ ተቋም ዶክትሪን የፖሊስ ተቋም ሙያዊ ብቃት እና የላቀ የሞራል ልዕልና ባላቸው አመራሮችና ሙያተኞች የተገነባ እንዲሆን ያስገድዳል። በዚህ የተነሳ ፖሊስን በሚመለከት የሚወጡ ህጎች፣ ደንቦች እና አሰራሮች ፖሊስን ከማንኛውም ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ የህዝቡን ሰላምና ደህንነት እንዲያስከብር የሚያስችሉ መሆን አለባቸው። አንድ የፖሊስ አባል የፖሊስነት ስልጣንና ኃላፊነት የሚኖረው በፖሊስነት ተመልምሎ ስልጠናውን ካጠናቀቀ፣ ቃለ-መሀላ ከፈጸመ እና የፖሊስ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችል ህጋዊ መታወቂያ ከተሰጠው በኋላ ነው።

ፖሊስ ከሰለጠነው ስልጠና፣ ከተሰጠው ኃላፊነትና ከሚከፍለው መስዋእትነት አኳያ አንድ የፖሊስ አባል ወደ ፖሊስ ተቋም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ከተቋሙ እስከሚገለልበት (መብትና ግዴታው) ጊዜ ድረስ እንዲሁም ከተገለለ በኋላ ያሉ ስርአቶች በህግ እና በአሰራር በግልጽ የታወቁ ይሆናሉ።

በአጠቃላይ የፖሊስ የስልጣን ምንጭ የሆነው የሀገሪቱ ህገ-መንግስት የሀገሪቱ ፖሊስ ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ እንዲደራጅ ያስገድዳል። ሙያውን መሰረት በማድረግ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ሁሉንም ዜጋ የማገልገል ግዴታ አለበት። በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ሳይንሳዊ እውቀቶችን የስራው መሰረት ያደረገ፣ በክህሎትና በስነምግባር ደረጃው በህዝብ የተመሰከረለት፣ ሙያውን የሚያከብርና በዚያውም ልክ የሚፈጽም ፖሊስ ይገነባል።

በሀገርአቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀራራቢ የፖሊስ ተቋምና አገልግሎት መገንባት የሚያስችል መሰረት የሚጥል እና የሚያጠናክርም ይሆናል። የፖሊስ አባላትን የመፈጸም አቅም የሚያሳድግ እና በተቋሙ እንዲቆዩ የሚያበረታታ ህግና ደንብ እንዲኖር ማድረግ ለፖሊስ ተልዕኮ ስኬት ወሳኞች ናቸው።

ከዚህ አጠቃላይ አስተሳሰብ በመነሳት የፖሊስን አሰራር የሚወስኑ ህጎችና ደንቦች የፖሊስን ተቋም ከማንኛውም የፖለቲካ ተፅዕኖ እና ጣልቃ ገብነት ነፃ በሚያደርግ መልኩ የሚያደራጁ፣ ሙያውን መሰረት በማድረግ የሚሰራ ነፃና የማያዳላ ተቋም በመፍጠር፣ በአህጉር እና አለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆን ፕሮፌሽናል ፖሊስ ለመገንባት የሚያስችሉ ይሆናሉ።

በተጨማሪም በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀራራቢ የፖሊስ አገልግሎት በመስጠት ጠንካራ አገራዊ ፖሊስ ለመገንባት መሰረት የሚጥልና የሚያጠናክር፣ የፖሊስ አመራሮችንና አባላትን የስራ ፍላጎትና አፈፃፀም የሚያሳድግ እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ተስፋ የሚሰጡና የሚያበረታቱ ህጎች፣ ደንቦችና አሰራሮች ይህን ዶክትሪን መነሻ በማድረግ ይቀረፃሉ።

## 4.1.2. የኢፌዲሪ ፖሊስ ተቋማት አደረጃጀት ቅርፅና ይዘት፣

አንድ ተቋም የሚቋቋመው ለተወሰኑ ዓላማዎች ነው። ይህንን ተልዕኮ ለመወጣት ደግሞ በርካታ መሰረታዊ ስራዎች መከናወን አለባቸው። እነዚህን ስራዎች ለመስራት ከተቋማዊ እሴቶችና ተልዕኮዎች በመነሳት ተቋሙ ግልጽ አደረጃጀት ይፈጥራል። አደረጃጀት በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች እና ቡድኖች ያላቸውን ተግባር፣ ኃላፊነት፣ ተጠሪነት፣ ስልጣን እና ግንኙነት በግልጽ የሚያሳይ ነው። አደረጃጀት ለአንድ ተቋም በተሰጠ ተልዕኮና በሚጠበቅ ውጤት መካከል ያለ አገናኝ ድልድይ እንጂ በራሱ ውጤት አይደለም።

የፖሊስ ሙያ ከባህሪው እና ከተልዕኮው አንጻር ድንበር አልባና አለም አቀፋዊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አደረጃጀቱና ስያሜው በብዙ ሀገሮች ተመሳሳይነት ያለው ነው። የፖሊስ ተልዕኮ በዋነኛነት ከዜጎች ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጋር እጅግ የተቆራኘ በመሆኑ ከሁሉ በፊት ውስጣዊና ውጫዊ የአደረጃጀት ስርአቱ በግልጽ አሰራርና ፍልስፍና መገንባት አለበት። የፖሊስ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በግልጽ የአደረጃጀት ስርዓት ካልተደራጁ የስራ ወይም የኃላፊነት ግጭት (Role conflict) እና የፍላጎት ወይም የጥቅሞች ግጭት (Conflict of Interest) በመፍጠር የተሰጣቸውን ተልዕኮ እና የተቋቋሙበትን አላማ በመሳት ላልተፈለገ ግጭትና መስዋዕትነት ይዳረጋሉ።

በሌላ በኩልም የፖሊስ አደረጃጀት ፍልስፍና የፌዴራል ስርዓቱን ቅርጽ ይከተላል። በፌዴራል ደረጃ የሚኖር የፖሊስ አደረጃጀት የሚኖረው ስልጣን በዋነኛነት ለፌዴራል ፍ/ቤቶች የተሰጡ የስልጣን ወሰኖችን መሰረት የሚደርግ ሲሆን የክልል ፐሊስ ስልጣንም ምንጩ ለክልል ፍ/ቤቶች በተሰጡ ስልጣን ወሰኖች ውስጥ ሆኖ ከየስራ ክፍሎቹ ለየት ያለ ባህርይና ተልዕኮ ጋር የተገናኘ ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የበርካታ አገራት የፖሊስ አደረጃጀት መርህ ውጣ ወረድ ያልበዛበት፣ ዝርግ፣ ለተገልጋዩ ቅርብና አመቺ በሆነ መልኩ የተዋቀረ ነው። አገልግሎት የጠየቀ ወይም ፍለጋ የመጣ ማንኛውም ሰው አገልገሎቱን ካለምንም ውጣ ወረድ እንዲያገኝ ማድረግ ተቀባይነትን ያጎናጽፋል፡፡ ከምንም በላይ ፖሊሳዊ አደረጃጀቶች ከማንኛውም የፖለቲካ ተጽዕኖ እና ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው እና የፖሊስ የሙያ ነጻነት እሳቤዎችን ይዘው እስከታችኛው የህዝብ አደረጃጀት ድረስ የተዘረጉና ቅርብ ሆነው እንዲደራጁ የሚደረግ ሲሆን ተቋሙም ለሁሉም ዜጎች እኩል አገልግሎት መስጠት እንዲችል ተደርጎ ይገነባል።

በተጨማሪም የብዙ አገራት ልምድ እንደሚያሳየው የፖሊስ ተቋም ተጠሪነት ለህዝብና በነጻ ምርጫ ለሚመሰረት መንግስት ይሆናል። ተልዕኳቸውን በተመለከተም የሙያ ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተለኪ የህዝብ ይሁንታ ያለው የአደረጃጀትና የተጠሪነት አስተሳሰቦችን መሰረት ያደርጋል። የፖሊስ ዋነኛና ኦፕሬሽናል ተልዕኮዎች በሆኑት በወንጀል መከላከል እና ምርመራ ስራዎች ጥብቅ የሆነ የዕዝ ሰንሰለትን (Chain of Command) እና የስራ ዲስፕሊን የሚከተል ይሆናል። ይህም ማለት በወንጀል መከላከል ስምሪት ላይ የሚደረግ የፖሊስ ፓትሮል (ቅኝት) ፣ ህገ ወጥ ሰልፎችን የመበተን

ስራዎች፤ የድንበር ጥበቃዎችና በግጭት ጊዜ የሚወሰዱ የመከላከል እርምጃዎች በዝንባሌያቸው ጥብቅ የእዝ ስርአት ይኖራቸዋል ።

የኢፌዲሪ ፖሊስ አደረጃጀት ቅርጽና ይዘት መሰረት የሚደርገው የህገ መንግስቱን የአደረጃጀት መርሆች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የፖሊስ አደረጃጀት ከባህሪይውና ከተልዕኮው አኳያ በአንድ በኩል ያልተማከለ ሲሆን በሌላ ገጹ ጥብቅ የእዝ ተዋረድን የተከተለ መሆንም ይገባዋል። ያልተማከለ የዕዝ ተዋረድ ማለት የፖሊስ አገልግሎት ለሚሰጥባቸው ክልሎች፤ ዞኖች ወረዳዎችና ቀበሌዎች ወዘተ… ውሳኔዎችንና ፖሊሳዊ ምላሾችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመስጠት ረገድ ፍጹም የሆነ ስልጣንን የሚያጎናጽፍና የፖሊስን አቅም የሚገነባ የዕዝተዋረድ ማለት ነው።

ለፌደራልና ለክልል በህግ በተሰጡ ህገ መንግስታዊ ተልእኮዎች መነሻነት የፖሊስ አደረጃጀት አጠቃላይ ዓላማና ግብ ኢትዮጵያዊ የሆነ የፖሊስ ተቋምን በመገንባት ላይ ያተኮረ ሆኖ የአደረጃጀቱ ቅርፅና ይዘቱ የፌዴራል አወቃቀሩን የተከተለ፣ ዴሞክራሲያዊና ያልተማከለ ይሆናል።

የስልጣን አሰጣጡ ለፖሊስ ከተሰጡ ስልጣኖች የሚመነጭ ሆኖ የመንግስትን የአስተዳደር አደረጃጃት እና ቅደም ተከተል ይዞ የተቀመረ ይሆናል። ይህም በፖሊስ አገልግሎት ውስጥ የስልጣን ደረጃ፤ ኃላፊነትና ተጠሪነት ከዚህ ዶክትሪን በሚቀዱ የማቋቋሚያ አዋጆች፣ ዝርዝር ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ይወሰናል።

በኢፌዴሪ ፖሊስ አደረጃጀት የፌዴራል ፖሊስ ለህገ-መንግስታዊ የፌዴራል ስርአቱ ዋና ዓላማ ለሆነው “አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ግንባታ” ዋስትና ለመስጠት፣ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር እንዲሁም የፌዴራል መንግስቱ በህገ መንግስቱ መሰረት ያወጣቸው ፖሊሳዊ አገር አቀፍ መመዘኛዎች እና ስታንዳርዶች ተፈጻሚነትን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል። የፖሊስ ሀገራዊ ጉባኤዎችን ይመራል፣ የጋራ ስትራቴጂዎችንም ያስፈጽማል ።

በሌላ በኩልም ክልሎች በተሰጣቸው ህገ-መንግስታዊ ስልጣን ውስጥ የሚሰጡት መደበኛ ፖሊሳዊ አገልግሎቶች እንደተጠበቁ ሆነው የጋራ ኦፕሬሽናል በሆኑ ጉዳዮች እና በፌዴራል የስልጣን ማዕቀፍ ውስጥ በሚወድቁ የወንጀል እና የህግ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ፖሊስን ስልጣን በውክልና ይዘው ሲሰሩ ውክልና ለወሰዱባቸው ጉዳዮች ለፌደራል ፖሊስ ተጠሪ ሆነው ሪፖርት የሚያደርጉበት ሞዴል ወይም የአሰራር ስርዓት ተከትለው ይደራጃሉ።

ይህም ለዕዝ አፈጻጸም እንዲሁም ግልጽ በሆነ የስራ ክፍፍል ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ባማከለ ሁኔታ ተጠሪነትን የማሳየት ሞዴል ዕሳቤን መሰረት ያደረገ ይሆናል። ይህ ማለት “የበላይና የበታች” የሚለውን አስተሳሰብ የያዘ ወይም የአዛዥና ታዛዥ አይነት ግንኙነትን የሚያንጻባርቅ ሳይሆን በህገ መንግስቱ መሰረት በመከባበር እና በመተማመን የመስራት አስተሳሰብን የሚያሳይ አደረጃጀት እና ግንኙነት ማለት ነው። ዝርዝር አፈጻጸሙም በፌዴራልና በክልል ፖሊስ ተቋማት መካከል በሚፈጠር ተቋማዊ እና ህጋዊ የአሰራር ስርዓት  መሰረት ይሆናል።

በሀገሪቱ ውስጥ የሚሰጡ የፖሊስ አገልግሎቶች አፈጻጸም በዋነኛነት በህዝብ፣ በመንግስት እንዲሁም ወጥና ነጻ በሆነ ሀገራዊ የፖሊስ ድጋፍና ቁጥጥር (National Inspection Team) እንዲገመገምና ግብረመልስ እንዲሰጠው ይደረጋል። በዚህ መነሻ የድጋፍና ቁጥጥር ስራን መሰረት ያደረገ ቡድን ተደራጅቶ በፖሊስ አሰራር ውስጥ የሚታዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን፤ የአሰራር ግድፈቶችን፤ የፖሊሲዊ አሰራር መርሆዎችን፤ ፖሊሳዊ ስነምግባርን፤ የህዝብ ንብረት አጠባበቅንና ጉቦንና አድሎአዊ አሰራሮችን ያያል።

የኢንስፔክሽን ቡድኑ ግብረ-መልስ የግልጽነት እና ተጠያቂነትን መርህ የተከተለ ሆኖ በሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኩሩ ግኝቶችን ለተጨማሪ ምርመራ ይመራል። ይህ ሪፖርት በማንኛውም ህጋዊ የግል እና የመንግስት የመገናኛ ብዙሀን ለህዝብ ግልጽ ይደረጋል።።

የሀገሪቱ የፖሊስ ተቋም የስራ ማዕከል የህዝብን ሰላምና ደህንነት በማስከበር በማህበራዊ መስተጋብሩ ያደገ እና የህግ የበላይነትን ለማስፈን የሚተጋ የፖሊስና ማህበረሰብ ተቋምን ማደራጀት ነው። ይህም ፖሊስን ለተሰጠው ተልዕኮ ዝግጁ እንዲሆን የሚያደርገው ነው። "በህዝብ ሰላምና ደህንነት ላይ ድርድር ሊኖር አይችልም" የሚለው ቋሚ የተቋሙ እምነት ነው። የኢፌዲሪ ፖሊስ አደረጃጀቱና ስያሜው መሰረታዊ መነሻ የሀገሪቱ ፖሊስ በሁሉም ስፍራ ማለትም በገጠርም ሆነ በከተማ የሚሰጣቸው ፖሊሳዊ አገልግሎቶች ተቀራራቢ ሆነው ተደራሽነት ያላቸውና ያለአድሎ በትክክል የሚፈጸሙ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት አደረጃጀቶች በተጨማሪ ከፖሊስ አወቃቀር ውጪ የሆነ የዜጎችን አቤቱታ የሚሰማ አማካሪ ቦርድና ገምጋሚ አካል (Civilian Complaint Review Board) ይቋቋማል። ይህ ቦርድ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነጻና በህዝብ አስተያየት የሚመረጥ ይሆናል ። ከስራው አንዱም በተለያዩ ጊዜያት ለሚከፈቱ የፖሊስ ጣቢያዎች ማረጋገጫን መስጠት ነው። የአፈጻጸም ተግባርና ኃላፊነቱ እንዲሁም አደረጃጀት እና የአፈጻጸም ስርዓቱ በዝርዝር ህግ ይወሰናል።

በተጨማሪም ከተቋሙ በክብር በጡረታ የሚገለሉ አባላት ሀገር አቀፍ የፖሊሶች የሙያ ማህበር (National Association of Police) እንዲያደራጁና ተቋሙን እንዲያማክሩ እና እንዲያግዙ ይበረታታሉ። በዚህ ቦርድ ውስጥም ለየት ያለ ሙያ ተኮር ሚናዎች ይኖራቸዋል። ለማህበር ምስረታቸውም መንግስት ልዩ ድጋፍ ያደረግላቸዋል።

## 4.2. የፖሊስ የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዶክትሪን፤

የሰው ሀብት ልማት የአንድ ተቋም ሰራተኞችን ግላዊም ሆነ ተቋማዊ ክህሎት፣ እውቀት እና ልምዳቸውን ለማዳበር የሚያግዝ ማእቀፍ ነው። የሰው ሀብት ልማት ትኩረት በተለያዩ የስልጠና ማዕቀፎች የላቀ የፖሊስ አባላት የስራ አፈጻጸም እንዲኖር የሚረዳ የፖሊስ ኃይል ወይም ቡድን መፍጠር ላይ ሆኖ አባላትም አላማቸውን ለማሳካት እንዲተጉ ያግዛቸዋል። የሰው ሐብት ልማት ዓላማ የግለሰቦችን

ፈጠራ የሚያበረታታ ሆኖ የመፈጸም አቅምን በማሻሻል የተቋምን የህግ ማስፈጸምና ፖሊሳዊ ተልዕኮ ውጤታማነትን ማሳደግ ነው።

የሰው ሐብት አስተዳደር ሂደት ሲሆን በውስጡም ሰራተኞችን መቅጠር፣ ማሰልጠን እና ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ማዘጋጀትን ይይዛል። የሰው ሐብት አስተዳደር ሰራተኞችን ለማቆየት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትንም ያካትታል። የአንድ ተቋም የሰው ሐብት ለተቋምም ሆነ ለአገር ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

በመሆኑም ይህንን የሰለጠነ የሰው ሐብት የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በጥብቅ ዲስፒሊን ይዞ በተገቢው ማስተዳደር ለአንድ ተቋም ውጤታማነት መሰረት ይሆናል።የሰው ሐብት አስተዳደር በውስጡ የሰው ሐብት ልማትን ያቅፋል። ከላይ የተጠቀሱትን ጽንሰ-ሃሳባዊ መነሻዎች በመያዝ የፖሊስ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር የሚከተሉትን እሳቤዎች ይይዛል።

## 4.2.1 የፖሊስ የሰው ሐብት ልማት፣ ምደባና አስተዳደር፣

ፖሊስ ተልእኮዎቹን ለማሳካት እና ራእዩን እውን ለማድረግ የሰው ሐብት ልማት እና አስተዳደር ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። የፖሊስ የሰው ሐብት ልማት እና አስተዳደር በትምህርት እና ስልጠና ይገነባል። የትምህርት እና ስልጠና ትኩረት ሶስቱን የትምህርት እና ስልጠና ማእቀፎች ማለትም እውቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ላይ ይሆናል።

### 4.2.1.1 የፖሊስ ሰው ሐብት ልማት፣

ሀ- የፖሊስ ምልመላና መረጣ፣

ምልመላ ማለት አንድ ተቋም የቅጥር መስፈርቱን የሚያሟሉ ተወዳዳሪዎችን በጊዜ በተገደበ ሁኔታ በበቂ ቁጥር እንዲያመለክቱ የሚጋብዝበት ሂደት ነው። መረጣ ማለት ደግሞ መስፈርቱን አሟልተው ካመለከቱት መካከል የተሻሉትን አመልካቾች በግልጽ የአሰራር ስርዓት የመምረጥ ሂደት ነው። የምልመላና መረጣ ግብ ተገቢ የሆኑ አመልካቾችን በተቀመጠው የመመልመያ መመዘኛ መሰረት መርጦ የተቋሙ ሀብት እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

የፖሊስን የምልመላ ስርዓት ልዩ ከሚያደርጉት ውስጥ የሙያው ባህርይ አንዱ ሲሆን በተለይም የውሳኔ ሰጪነትን፣ የአገልግሎት ፈላጊዎች ብዛትን፣ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጫናዎችን ይጨምራል። የፖሊስ ምልመላና መረጣ ሒደት እንጂ በአንድ ጊዜ የሚጠናቀቅ ስራ አይደለም።

በዚህ ዶክትሪን የፖሊስ ምልመላና መረጣ የፖሊስን የዕለት ተዕለት ስራ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ብቻ ሳይሆን ተቋሙን በብቃት ለማስቀጠል እንዲቻል የወደፊት የተቋሙን ስትራቴጂያዊ መሪዎችን

የማፍራት የላቀ ራዕይና ዓላማን ጭምር ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡ ይህም የምልመላና መረጣ ስራን ለፖሊሳዊ ሙያ መሰረት ያደርገዋል፡፡ የምልመላ እና መረጣ ሂደት ብዝሀነትንም (የማንነት፣ የጾታ፣ የሃይማኖት ወዘተ) መሰረት አድርጎ መከናወን ይገባዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተለያየ ሙያ ባለቤት የሆኑ አባላትን በጥንቃቄ የመመልመል እና የመምረጥ ስራ ማከናወን የፖሊስ ተቋምን የዘርፈ ብዙ ሙያዎች ባለቤት ያደርገዋል፡፡ በምልመላና መረጣ ሂደት ውስጥ አልፎ ለፖሊሳዊ ትምህርትና ስልጠና እጩ የሚሆነው አመልካች የቤተሰብንና የማህበረሰቡን ይሁንታ ማግኘት የሚችል ብቻ ነው፡፡ የሀገራችን ፖሊስ በፖሊስነት ተመልምለው በግልጽ መመዘኛ ተለክተው በሚገቡ ዕጩዎች እንጂ ከሌላ ተልዕኮ ጋር በሚገቡ "ሰዎች" የሚገነባ አይሆንም፡፡

በምልመላና መረጣ ሂደት በተለይ የጾታ እኩልነት የተከበረ ይሆናል፡፡ የጾታ ምጥጥን በፖሊስ ስራ ውስጥ ቁልፍ ሲሆን በተለይም የሴቶች ተሳትፎ በልዩ ሁኔታ ይታያል፡፡ ምክንያቱም መብቶችን፤ ኃላፊነቶችንና ዕድሎችን መጠቀም ወንድ ወይም ሴት ሆኖ መፈጠርን አይጠይቅም፡፡ በዚህ ዶክትሪን ውስጥ በምልመላ፤ በማቆየትና በተለያዩ የፖሊስ መዋቅሮች ውስጥ የጾታ እኩልነት ትርጉም ባለው ሁኔታ ይታያል፡፡ በገለልተኛ ቡድን ኢንስፔክሽንም ይረጋገጣል፡፡

ብዝሀነትንና እኩልነትን በአዎንታዊ መልኩ ለማሳደግ በጎ አመለካከቶች በፖሊስ ውስጥ የአስተሳሰብ መነሻ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም በጎ የሆኑ የማበረታቻ ማዕቀፎች ላይ በማተኮር በምልመላ ጊዜ ሴቶችን የሚያበረታቱ የምልመላ ቅስቀሳዎችን፣ጾታ ተኮር የሆኑ ፕሮግራሞችን፣ ስልጠናዎችንና የተሳትፎ ማበረታቻዎችን ይጨምራል፡፡ የሴቶች ተሳትፎ በጥመርታ (Ratio) ይወሰናል ፡፡

የምልመላና መረጣ ሒደቱ በግልፅ በተቀመጠ መመዘኛ በአገር ደረጃ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ይከናወናል፡፡ አዲስ የፖሊስ ምልመላና መረጣ የሚካሄደው የአገሪቱን የፖሊስ አባላት ነባራዊ ፍላጎት እና አገር አቀፍ ፖሊሳዊ ስታንዳርዶችን (National Police Standards) መሰረት ባደረገ መልኩ በዝርዝር የፍላጎት ጥናት እና አገራዊ የፖሊስ የሰው ኃብት ልማት ስትራቴጂ ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡ ለዚህም የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር ቁጥጥር ለማድረግ የሚረዳ አንድ የሰው ሀብት የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ይደረጃል ፡፡

## ለ. የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና፣

የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ስርዓታችን በዓለም አቀፍ የፖሊስ ዕድገት የተቃኘ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀራራቢ የትምህርትና ስልጠና ስርዓት መዘርጋት የሚያስችል፣ የሳይበር አሸባሪነትንና እና ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል ይሆናል፡፡ በሌላ በኩልም የፖሊስ አመራሩን እውቀትና ክህሎት የሚያሳድግና ፖሊሳዊ ስነ - ምግባርን የሚያበለፅግ እንዲሆን ሆኖ ይቀረጻል፡፡ በተጨማሪም ነፃ፣ በራሱ የሚተማመን እና ሙያዊ ብቃት ያለው (Professsional Police) ለመገንባት በሚያስችል መንገድ ይቀረፃል፡፡

የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ፍልስፍናዎች መሰረት የሚያደርጉት የፖሊስ እሴቶች እና መርሆዎችን ሲሆን በእነዚህ ላይ መስራት ሀገራዊ መግባባትን ከማሳደግ በላይ ኢትዮጵያዊ ቁመና ያለው የህዝብ ፖሊስ እንዲኖር ማድረግ ያስችላል። የፍልስፍናው መሪ መሰረትም ፖሊሳዊ ጠቢብነትን መሻት (Seek Police Wisdom) ፣ፖሊሳዊ ምሁርነትን ማሳደግ (Eleviate Police Intelect) እና ህዝብን ማገልገልና (Serving Humanity) ሰብአዊነትን መለበስ የሚሉት ናቸው። እነዚህ የፍልስፍና መሰረቶች የፖሊስን ትምህርትና ስልጠና ሳቢ እና ተመራጭ ያደርጉታል። እነዚህ ፍልስፍናዎችም የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ቁልፍ መርሆዎችም ይሆናሉ።

የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ፍልስፍናዎች የፖሊስ አባላትን የፈጠራ አቅም ማሳደግ፣ በአእምሮው እና በአካል ብቃቱ የዳበረ የፖሊስ አባል ማፍራት፣ ስነ ምግባር በተሞላበት ሁኔታ ፖሊሳዊ ኃላፊነትን መወጣት፣ የችግር አፈታት ክህሎት ማሳደግና ፖሊሳዊ ፍቅርን በማላበስ የህዝብ አገልጋይነት ስሜትን ማሳደግ ናቸው።

በትምህርትና ስልጠና የሚገኙ ዕውቀቶችና ክህሎቶች የፖሊስ አባላትን  የሰላም አምጪ አባት፣ የማህበረሰብ ችግርን ለመፍታት የሚረዱ ለየት ያሉ ሀሳቦችን አመንጪ፣ የስነ ልቦና አማካሪና የማህበረሰብ ሳይንስ ተመራማሪ በማድረግ የዘርፈ ብዙ ዕውቀቶች ባለቤቶች ያደርጓቸዋል።

የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና መሰረታዊ ስልጠናዎች ማለትም የምልምል እና የካዴት ስልጠናዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ የሚሰጥ ሲሆን ትምህርትና ስልጠናው የተቋሙን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እና ከፖሊስ ሙያ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያለው ይሆናል። የትምህርትና ስልጠና ሂደቱ ቁጥር ላይ ከማተኮር ይልቅ ጥራት ያላቸው እና ለሙያቸው ቀናዒ የሆኑ የፖሊስ አባላትን በማፍራት ለማህበረሰቡ ተገቢውን ግልጋሎት ማበርከት ላይ ያተኩራል። በፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ውስጥ የሚያልፉ አባላት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከትምህርት ደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የስራ ምደባ ያገኛሉ።

ትምህርትና ስልጠናው የአባላትን የፈጠራ ችሎታ በማዳበር በማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ላይ በሚደረጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትብብሮች ላይ አሻራን በማኖር አጋርነትን ማበልጸግና ፖሊስንና ማህበረሰበን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገርን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል። ለዚህም ሀገር በቀል የሆኑ እና አውድን መሰረት ያደረጉ (የገጠሩን እና የከተማውን ባህል፣ አኗኗርና ስለ ልቦና ማእከል ያደረገ) የአካባቢ ደህንነት ጥበቃና የፓትሮል አደራረግ ዘዴዎች፣ ዕውቀቶች፣ ክህሎቶችና ጥበብ በፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ውስጥ ይካተታሉ።

በሌላ በኩልም ለወንጀል መፈጠር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን እኩይ ተግባሮችን መከላከልና የማህበረሰቡን ንቃተ - ህግ በማሻሻል ላይ የሚያተኩር እና በማህበረሰብ አገልግሎት ቅኝት የሚሰራ ነው። ፖሊስ የሚመራው በፖሊስ ሣይንስ ዕውቀት ነው። ይህ ዕውቀት የሚገኘው ከፖሊስ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ነው። በዚህ መንገድ ባልተገኘ ዕውቀት ፖሊስ መሆን ወይም የፖሊስ ተቋምን መምራት አይቻልም።

### ሐ. የፖሊስ ጥናትና ምርምር፣

የፖሊስ ጥናትና ምርምር ዘዴ ሁለት የፍልስፍና ጫፎችን ወይም የምርምር ፓራዳይሞችን ይከተላል። እነርሱም ፖዘቲቭዚምና ፖስት ፖዘቲቪዚም፤ (Positivisim and Postpositivims) እና ኢንተርፕሪቲዝምና ኮንስትራክቲቪዚም (Interpretisim and Constructivsim) ናቸው። የፖሊስ ጥናትና ምርምር በሁለቱም ፓራዳይሞች ላይ ቢመሰረት አንጻራዊ አረዳድን ወይም ጥልቅ የሆነ መረጃን ለማጠናቀር ይረዳሉ የሚል የፖሊስ አባላትና የስነ ወንጀል ተመራማሪዎች ስምምነትን የተከተለ ይሆናል።

በፖሊስ በሚካሄዱ ጥናቶችና ምርምሮች በመሬት ላይ ያለ ዕውነታን በተመለከተ በአንድ ጉዳይ ላይ የሰዎችን አረዳድ በጥልቀት ለማግኘት መጣሩ ከቀመራዊው ዓይነት በይዘቱ ሻል ያለ ነው ተብሎ የሚወሰደውን አለም አቀፋዊ ስምምነት ከጥናት ስልቶች ውስጥ ይካታተሉ።

ከላይ የተጠቀሱት የጥናትና ምርምር ፓራዳይሞች የፖሊስን እና የማህበረሰብ ግንኙነትን በማጠናከር ረገድ ተግዳሮቶች ሆነው የሚታዩ ችግሮችን በጥልቀትና ሳይንሳዊ በሆነ የጥናትና ምርምር ዘዴ ለመለየት የሚረዱ ናቸው።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ፖሊስ የጥናትና ምርምር ፍልስፍና መነሻ የፓራዳይሞች ቁልፍ ሀሳቦች ሆነው ተወስደዋል። ለዚህም ዋናው ምክንያት የፖሊስ ሙያ ከህግና ሌሎች የማህበረሰብ ሣይንስ ትምህርቶች በአብዛኛው እንዲሁም ከተፈጥሮአዊ ሳይንስ በከፊል ወስዶ አንድ የሙያ ዲስፕሊን ሆኖ የወጣ በመሆኑ የሁለቱም ፓራዳይሞች አቀንቃኝ መሆን ተገቢ በመሆኑ ነው ።

በአጠቃላይ በሁለቱ ፓራዳይሞች ሀሳብ ላይ በመመስረት በሀሳዊ፣ ቀመራዊና ቅይጣዊ በሆነ ስልት ላይ ያረፈ የጥናትና ምርምር መስክን ያካተተ የፖሊስ ጥናትና ምርመር ቁልፉ የዚህ ዶክትሪን ሀሳብ ነው፡ ፡ በፖሊስ ውስጥ የሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች የመጨረሻው ውጤት ወቅታዊ ችግሮችን የሚፈታ፣ አዳዲስ ሀገራዊ እውቀቶችን የሚያመነጭ፤ ክፍተቶችን የሚሞላ፤ ለፖሊሲ አውጪዎች ግብአት የሚሆኑ መሆን አለባቸው። የምርምር አካባቢዎችም በዋነኛነት፤ የፖሊስን አገልግሎት ጥራትና በማህበረሰቡ ውስጥ የፖሊስን ሚና፣ የኦፕሬሽን ውጤታማነት፣ በብዝሀ ማህበረሰብ ውስጥ የፖሊስ ሚና፣ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና፣ የፎረንሲክ ሳይንስ፣ ወዘተ…በሚመረምሩ ላይ ያተኩራል።

## 4.2.1.2 የፖሊስ የሰው ሀብት ምደባ፣

የፖሊስ አመራር እና አባላት ምደባ ብቃትን መሰረት ያደረገ ሆኖ ማእረግን፣ የትምህርት ደረጃን፣ የስራ ልምድን፣ስነ ምግባርንና የስራ ምዘና ውጤትን ያካትታል። ምደባው “ትክክለኛው ሰው በተገቢው ቦታ” በሚለው መርህ መሰረት አገልግሎቶቹንና የፖሊስ አባላትን ለማገናኘት ያለመ ይሆናል።

በአንድ አካባቢ የሚኖር የፖሊስ አባላት ስምሪት ምጣኔ የአካባቢውን የህዝብ ብዛትና የማንነት ስብጥር፣ የወንጀል ስጋት እና መልካዓ ምድራዊ አቀማመጥን ታሳቢ ያደርጋል። በሌላ በኩልም የፖሊስ አባላት ምደባ ምጣኔ 85% በወንጀል መከላከል እና የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ላይ በቀጥታ መሳተፍን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

## 4.2.1.3 የፖሊስ ሰው ሀብት አስተዳደር፣

አንድ ተቋም በየትኛውም ደረጃ የሚቀጥራቸውን ሰራተኞች በተለያየ መንገድ ለማቆየት ጥረት ካላደረገና የስራ ዋስትና ካላረጋገጠ የስራ ተነሳሽነት ከማጣት ጀምሮ ስራ እስከማቋረጥ የሚደርስ ውሳኔ ያስወስናል። በአግባቡ ሰልጥኖና ተገንብቶ ለስራ ለተዘጋጀ ሰራተኛ ጥሩ የስራ አካባቢ መፍጠርና ለሚሰራው ስራና ውጤት ዋስትና መስጠት ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ያግዘዋል።

የፖሊስ ሰው ሀብት አስተዳዳር እሳቤ የሰው ሃብት ፍልሰትን በመከላከልና የስራ ዋስትና በመስጠት ተቋሙን ብቃትና ልምድ ባላቸው የፖሊስ አባላት ማሻሻል ነው። ከዚህ አንፃር የሰው ሀብት አስተዳዳር የአባላትን መብቶች እና ጥቅሞች ለማስከበር እንዲሁም ግዴታቸውን በተገቢው መንገድ እንዲወጡ ለማስቻል የሚረዱ ግልፅ አሰራሮችን በየደረጃው ባሉ በሁሉም የተቋሙ አደረጃጀቶች በማስፈን የሚከናወን ተግባር ነው።

ይህ መሆኑ በፖሊስ ተቋም ውስጥ ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት እና ምቹ የስራ ቦታ እንዲኖር ያደርጋል። በተጨማሪም ማንኛውም የፖሊስ አመራርና አባል ያለዉን ቅሬታ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ የሚችልበት ግልፅ አሰራር ይዘረጋል።

## 4.2.2. የፖሊስ ማዕረግ አሰጣጥና የዕዝ ጠገግ (Chain of Command)፣

በአለማችን በብዙ ሀገሮች የፖሊስ ተቋም የዕዝ ጠገግ (Chain of Command) ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ተመሳሳይ ነው። በሌላ በኩል የዕዝ ጠገግ/ሰንሰለት ከተሰጠው ማዕረግ ደረጃ ጋር የተያያዘ ወይም የተቆራኘ ነው። በእያንዳንዱ ማዕረግና የደረጃ እድገት የተሰጠን ኃላፊነት፣ ተጠያቂነት እና የመፈጸም ብቃትን የሚያሳይ ነው።

የጠበቀ የዕዝ ሰንሰለት በተቋሙ ውስጥ እና በሰራተኛው መካከል ያለውን ዲስፕሊንና የኃላፊነት ተዋረድ በግልጽ የሚያሳይ ነው። በፖሊስ ውስጥ በግልጽ የሚታይ የዕዝ ጠገግ እና ዲስፕሊን ከሌለ የተቋሙን እሴቶች ከመሸርሸሩም በላይ  በዜጎች ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ ሰፊ ጥሰትን  ሊያስከትል ይችላል።

የፖሊስ ማዕረግ አንድ የፖሊስ አባል በተቋሙ ውስጥ ያለውን የስራ ኃላፊነት፣ የስልጣን ደረጃ፣ መብትና ግዴታ በግልጽ የሚያሳይ ቅደም ተከተል ያለው በክንድና በትከሻ ላይ በክብር የሚቀመጥ መገለጫ ማዕረግ ነው። ምልክት ግን አይደለም ።

በዚህ ዶክትሪን የፖሊስ ማዕረግ ቅደም ተከተል የማዕረግ ብልጫ መኖር ወይም አቻ ማዕረግ ኖሮ የሹመት ቅድሚያ መኖር ወይም አቻ ማዕረግና ሹመት ኖሮት በስራው ኃላፊነት ከፍ ያለ መሆን ወይም አቻ ማዕረግ ሹመትና የስራ ኃላፊነት ኖሮ በቅጥር ዘመን መብለጥ ነው፡፡ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል አንድ የፖሊስ ማዕረግና የስራ ኃላፊነት መገለጫው አንድ ነው፡፡ የፖሊስ የማዕረግ አሰጣጥ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከታች ወደላይ እያደገ የሚሄድ ነው፡፡

የፖሊስ ማዕረግ ፍልስፍና ወይም ዋናው እሳቤ በሀገራችን ፖሊስ ውስጥ የኃላፊነት ደረጃንና ተዋረድን (Chain of Command) በግልጽ ለማሳየት ነው፡፡ የኢፌዲሪ ፖሊስ ማእረግ ከአለም አቀፍ የፖሊስ ማዕረጎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው እና ማህበረሰቡ በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችል ስያሜ ያለው መሆን አለበት ፡፡

ሌላው የማዕረጉ ፍልስፍና አንድ የፖሊስ አባል አሁን በያዘው ማዕረግ እና ሀላፊነት ውጤታማ ስለመሆኑ ምስክርነት የሚሰጥበትም ነው፡፡ የፖሊስ ማዕረግ በፈተና እና ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚሰጥ የፖሊስ ማዕረግ አይኖርም፡፡ የማዕረግ አሰጣጥና ስልቶች በህግ የሚወሰን ይሆናል ፡፡

## 4.2.3. የፖሊስ ስነ- ምግባርና ስብዕና (Police Ethics) ግንባታ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፖሊስ ሚና ህግን ከማስከበር በተጓዳኝ ማህበራዊ አገልግሎትን ለማህበረሰቡ መስጠትን ይጨምራል፡፡ በማህበረሰብና ፖሊስ መካከል የሚገነቡ አዎንታዊ ግንኙነቶች መሰረት ህዝብ በፖሊስ ላይ ያለው ዕምነትና አመለካከት ነው፡፡

በጎ እምነትና አመለካከት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ለሰው ልጆች የሰጣቸውን ሰብአዊ ክብሮች፣ መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን በመጠበቅ ረገድ የፖሊስ አባላት ባላቸው ጽናትና ቁርጠኝነት ላይ ያርፋል፡፡ ይህም ከፖሊስ ስነምግባር በመነሳት መዳረሻውን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሚገኙ የስብዕና ግንባታ መርሆዎች ላይ ያደርጋል፡፡

የስነ-ምግባር ፍልስፍና ማጠንጠኛው ማንኛውም ነገር በትክክለኛው መንገድ መፈጸሙ ነው፡፡ በስነ ምግባር ፍልስፍና ትክክለኛ ነገር ማለት በማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያገኙ እሴቶችን ያካተተ ድምር የእንቅስቃሴዎች ወይም የድርጊቶች ውጤት ነው፡፡ ከስነ ምግባር መርሆዎች ውስጥ ገዥ አስተሳሰቦች ናቸው ተብለው ከሚወሰዱ ሚዛን ደፊ ሀሳቦች መካከል አንዱ ‘ ’ ትክክለኛ ነገር ስህተት የመሆን ዕድል የለውም ወይም ሁል ጊዜም ትክክለኛ ነው” የሚለው ሲሆን ‘ ’ ስህተት ደግሞ ትክክል የመሆን ዕድሉ የመነመነ ወይም ስህተት ምንጊዜም ስህተት ነው” ከሚል የሚነሳ አለምአቀፍ ዕውነታን ይጨምራል፡፡

የፖሊስ አባላት ትክክለኛውን ነገር ለመፈጸም ሳይችሉ ሲቀሩ ወይም ስህተት መሆኑን እያወቁ ሲፈጽሙ በፖሊሳዊ ስነ ምግባር ክህደት እንደመፈጸም ያስቆጥራል፡፡ ለፖሊስ ተቋምና አባላት የተሠጡ ስልጣኖች ለማንም ተቋም ያልተሰጡ ናቸው፡፡ ልዩ የሚያደረጋቸውም ለፖሊስ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ህግን የማስከበር ስልጣን የሚሰጡ መሆናቸው ነው፡፡

ይህ ስልጣንም የሰዎችን የመንቀሳቀስ መብት ከማገድ ጀምሮ ምክንያታዊ የሆነ ሀይልን እስከመጠቀምና መኖሪያ ቤቶች ድረስ ገብቶ ብርብራን እስከማደረግ ይደርሳል። ይህ በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ከሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ማረሚያ ቤቶች በላይ ህዝብ ከፖሊስ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚገናኝ ከፍተኛ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ያሳያል።

የፖሊስ ስነ-ምግባር ፍልስፍና መነሻው ለማህበረሰብ አገልግሎት ከመስጠት፣ ህግን ከማስከበር እና ወንጀልን ከመቆጣጠር የአገልግሎት አስተሳሰብ ይጀምራል። በጥቂት ፖሊሶች የሚፈጸሙ የስነ-ምግባር ጥሰቶች የአጠቃላይ የፖሊስ አባላትን ጥላሸት ያለብሳል (Few Bad Apples Hurt Everyone's Reputation) ። ይህም በፖሊስ የገጽታ ግንባታና የፖሊስ እና የህዝብ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደር በላይ የህዝብ ተቀባይነትን ያሳጣል ።

ብዙ ሀገራት የፖሊስ ስነ-ምግባር ደንብ (Code of Ethics) አላቸው፡፡ የፖሊስ የስነ ምግባር ኮዶች መነሻ የፖሊስ አባላትን የራስ መተማመን ማጎልበት ሲሆን የስራ ውጤታማነትን ተአማኒ በሆነ መልኩ መለካትን ያስቻላል።

በሀገራችን የፖሊስ ስነ-ምግባር የሚካተቱ ሀሳቦች መነሻቸው በፖሊስ እና ማህበረሰብ ግንኙነትና ዲሞክራቲክ ፖሊሲንግን በማዳበር ላይ ያጠነጠኑ ሆነው በዕለት ተዕለት ተግባራት በተለይም ለጥቃት ተጋላጫ የሆኑ የማህበረሰብ አካላትንና ሌሎችንም በማስተናገድ ረገድ የፖሊስን መልካም ስምና ዝና ከሚያጠፉ እኩይ ተግባራት በመራቅ የአካባቢው አርዓያና ተምሳሌት ሆኖ መታየትን እንዲሁም በፖሊሱ የራስ መተማመንንና የስራ ዋስትና ያካትታል።

በማንኛውም የህግ ማስከበር ተግባር ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች የሰዎችን ሰብአዊ መብቶች የማይጋፉ መሆን አለባቸው። የፖሊስ አባላት በፖሊሳዊ ስነ-ምግባር በመታነጽ ስብዕናን ማጎልበትና ማሳደግን እንደ አንድ የብቃት ማሳደጊያ ዘዴ መጠቀም የስራቸው አካል ማድረግ አለባቸው። የፖሊስ አባል በመሆን የተፈጠረላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም ያወቁትን ሚስጥሮችና የኦፕሬሽን ዕቅዶች በጥብቅ ዲስፕሊን መጠበቅ ይገባቸዋል።

## 4.3. የፖሊስ ተቋማት የግንኙነት ዶክትሪን፣

የፖሊስ ተቋማት ግንኙነት ስንል በዋነኛነት ፖሊስ የተሰጡትን ተልዕኮዎች በብቃት ለመፈፀም የሚያስችሉ የሌሎች ተቋማትንና የህብረተሰቡን አቅም፣ ትብብርና ድጋፍ ለማግኘት፣ የተሻሉ ልምድና አሰራሮችን ለመቅሰም የሚያስችል ስርዓት ነው። በሌላ በኩልም ዓለም የደረሰበትን የፖሊስ የዕድገት ደረጃ ወደ አገራችን በማምጣት እና ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ተደራሽና ጥራት ያለው የፖሊስ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አሰራር መዘርጋትም ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከአለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅትና ከአገራት የፖሊስ ተቋማት ጋር በትብብር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መመስረት ያስፈልጋል ።

የዓለማችን ታሪክ የሚያሳየው ዘመናዊ ፖሊስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ “ፖሊስ የህዝብ፣ ህዝብ ደግሞ የፖሊስ” የሚለውን ፍልስፍና ያለጠንካራ የፖሊስና ህብረተሰብ ግንኙነት እውን ማድረግ እንደማይቻል ነው፡፡ የፖሊስ ሙያ ዓለማቀፋዊ ይዘት ያለውና አንድ አገር ለብቻው ጀምሮ የማይጨርሰው ተግባር ነው፡፡

ስለዚህም የሀገራትን የጋራ ትብብርና መደጋገፍ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የውስጥም ሆነ የውጭ ግንኙነቶች የፖሊስ ተቋሙን ውጤታማነት በሚያጎለብት መልኩ መመስረት ይኖርባቸዋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ የፖሊስ ተቋማት የየራሳቸው ተልዕኮና ግብ ያላቸው ቢሆንም ዋናውና ሊደረስበት የሚገባው ግብ ግን በትብብርና በፅኑ መሰረት ላይ የተገነባ ሁለንተናዊ ግንኙነት በመፍጠር ዘመኑን የሚመጥን ጠንካራ ሀገራዊ የፖሊስ ተቋም መገንባት መሆን አለበት፡፡

## 4.3.1. በፖሊስ ተቋምና በህብረተሰቡ መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት፣

ፖሊስ የተሰጡትን ተልዕኮዎችን ለመወጣት በሚያደርገው ጥረት ከሕብረተሰቡ ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር አለበት፡፡ የፖሊስ እና የሕብረተሰብ ግንኙነት መሰረቱ አገልግሎት በሚሰጥ እና በሚቀበል ሁለት አካላት መካከል የሚኖር የትብብር ግንኙነት ነው፡፡

በፖሊስ ተቋማት እና በማሕበረሰቡ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት መነሻ “ፖሊስ ህዝብ ነው፤ ህዝብም ፖሊስ ነው” በሚለው አለም አቀፍ መርሆ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የዚህ መርሆ መሰረታዊ ሀሳቦች የሚያጠነጥኑት እያንዳንዱ የሕብረተሰብ አባል እንደ ፖሊስ ሆኖ እንዲሰራ (self-policing)፣ ለማድረግ በቅድሚያ በሕብረተሰቡና የፖሊስ አባላት መካከል ጥላቻና የተዛባ አረዳድ እንዳይኖርና ጤናማ የማህበረሰብ መስተጋብር በመኖሪያ አካባቢዎች፣ በማህበረሰብ ውስጥ በሚፈጠሩ የግንኙነትና የአብሮነት ትስስር መነሻው መተሳሰብንና መከባበርን ለማጠናከር ያለመ እንዲሆን በማድረግ ወንጀልንና በማህበረሰበ ተቀባይነት የሌላቸው ባህርያትን መታደግ በሚሉት ላይ የሚያርፍ ሀሳብ ነው፡፡

በፖሊስ ተቋማት እና በሕብረተሰቡ መካከል በመተማመን ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ግንኙነት መፈጠር የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ እና ውጤታማ የፖሊስ አገልግሎትን ለመስጠት ወሳኝ መሰረት ነው፡፡ በፖሊስ እና በሕብረተሰቡ መካከል የሚኖረው ግንኙነት የተሳለጠ መሆን አለበት፡፡

ይህም ሲባል በአንድ በኩል ሕብረተሰቡ ፖሊስ “ይጠብቀኛል” “ያገለግለኛል” ብሎ እንዲያስብ በሌላ በኩል ደግሞ ፖሊስ ውጤታማ ስራ ለመስራት የሕብረተሰቡን ድጋፍ እና ትብብር እንዲሻ መሆን አለበት፡፡ ጠንካራ ግንኙነት መፍጠሩ ፖሊስ ማሕበራዊ አገልግሎትን፣ ወንጀል መከላከልን እና የተፈጸመን ወንጀል መመርመርን በማህበረሰብ ተሳትፎና ሙያዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን ያግዘዋል፡፡

ያለ ሕብረተሰቡ ሙሉ ተሳትፎና እገዛ የፖሊስ ተግባራት ውጤታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ በመረዳት ሕብረተሰቡ በፖሊስ ላይ ሙሉ እምነት እንዲኖረው የፖሊስ ተቋማት ኃላፊነቱን በመውሰድ በትኩረት መስራት አለባቸው። የፖሊስ አባላትም የሚያገለግሉትን ሕብረተሰብ ወንጀል መከላከል ፤ በችግር አለያየትና መፍትሄ ላይ አካል አድርገው መውሰድ ይኖርባቸዋል።

በተቃራኒው በፖሊስ ተቋማት እና በማሕበረሰቡ መካከል የሚኖር ግንኙነት በመተማማን ላይ ካልተመሰረተ ፖሊስ ተልዕኮውን መወጣት አይችልም። ይህም የሆነበት ምክንያት ፖሊስ ያለሕብረተሰብ ተሳትፎ ወንጀል መከላከልም ሆነ የተፈጸመን ወንጀል በመመርመር ውጤት ማምጣት ባለመቻሉ ነው። በፖሊስ አባላት እና በማሕበረሰብ አባላት መካከል የሚፈጠር በመርህ ላይ የተመሰረተ ግለሰባዊ ግንኙነትም መተማመንን ይፈጥራል።

ፖሊስ ከሕብረተሰቡ ጋር በጋራ የሚሰራበት ሁኔታ እና ወንጀልን ለመከላከል የሚያደርገው ጥረት ግልጽነት በተሞላበት መንገድ መከናወን አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ወንጀልን በመከላለከል ሒደት ሐላፊነቱን ሲወጣ የሚሰራበትን ማሕበረሰብ ብዛሃነት፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች እንዲሁም የማሕበረሰቡን አባላት ሰብዓዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች በማክበር እና በማስከበር ጭምር መሆን አለበት። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ህግን በማስከበርና ስርአትን በማስፈን ረገድ ጥብቅ ስርዓት የሚከተል ሲሆን በተለይምሙያዊ ነጻነቱንና ፖሊሳዊ ስነምግባሩን በማንኛውም መልኩ ቢሆን ለድርድር አያቀርብም።

ከዚህም በተጨማሪ ሕብረተሰቡ በፖሊስ ተቋምና አባላት የምዘና ሒደት፣ እድገት እና በፖሊስ አባላት ላይ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ አስተያየት በመስጠት የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት።

## 4.3.2. የፖሊስ ተቋማት ከመስተዳድር አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፣

በፌደራልና በክልል መስተዳድሮች ፖሊስ ተቋማት መካከል የሚኖረው ግንኙነት መነሻ እና መሰረት “አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት” ተብሎ በኢፌዲሪን ህገ መንግስት የተቀመጠውን ራዕይና የመከባበርና የመተማመን ዓላማዎች ናቸው። በሌላ በኩልም በፌዴራልና በክልል ፖሊስ መካከል የሚደረግ ግንኙነት አጠቃላይ መዳረሻ ውጤታማ ፖሊሳዊ አገልግሎት በመስጠት ህዝብ እና መንግስት እምነት የሚጥልበት ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ፖሊስ በሀገር ደረጃ መገንባት ይሆናል።

በህዝብ ዕርካታ ላይ መሰረተ ያደረገ የፖሊስ አገልግሎት ምዘና ዋና የምዘና አቅጣጫ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወንጀል መከላከል፣ ምርመራ፣ ትራፊክ፣ የሰው ሀይል አጠቃቀም ስኬት በተጨማሪ የተለያዩ የኦፕሬሽንና ድጋፍ ክፍሎች እና ከክልል የፖሊስ ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት በሚመዘገቡ ደረጃዎች ጭምር ይሆናል። በህገ መንግስቱ ለፌዴራልና ለክልል መስተዳድሮች ተለይተው የተሰጡ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ፖሊሳዊ ተልዕኮ በባህሪው ድንበር አልባ መሆኑን ከግንዛቤ

በማስገባት የጋራ መግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት እና የህግ ድጋፍ (Standard & Framework Power) እንዲኖረው በማድረግ በትብብርና በአጋርነት መፈጸም አለበት።

በዚህም በፌደራልና በክልል ፖሊስ ተቋማት መካከል የሚገነባው ግንኙነት ዓላማ በሀገር ደረጃ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ፍትህ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ሲሆን ከግንኙነታቸው ውስጥ አንዱ በፌደራል የፖሊስ ተቋም ውስጥ የብዝሀነት ጥያቄ የሚመለስበት ይሆናል።

የፌዴራልም ሆነ የክልል አካላት የፖሊስ ተቋማት ሰላምና ልማት የተያያዙና የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ተገንዝበው ከፀጥታ ስጋት ነፃ የሆነ አካባቢ እንዲኖር ቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ። መንግስትና ህዝብ የሚያቅዳቸውና የሚተገብራቸው የልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት በአካባቢው በሚኖረው ሰላምና ፀጥታ የሚወሰን በመሆኑ ፖሊስ በፍፁም የሃላፊነት መንፈስ በግልጽ የግንኙነት ስርዓት በታቀደና በተደራጀ ሁኔታ በመስራት የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ አገራዊ ኃላፊነቱን ይወጣል።

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚደራጁ የፖሊስ ተቋማት ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ በሆነ ቦታ ሊቋቋሙና የተሟላ ግብዓት ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም የፖሊስ የሰው ሃይል የሚቀረፅባቸው የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ወደ ተቋሙ የሚገቡትን ወጣቶች የወደፊት ተስፋ በሚያለመልሙና ለስራ በሚያዘጋጅ ሁኔታ እንዲደራጁ ይደረጋል።

በሌላ በኩልም የአካባቢ መስተዳድሮች የፖሊስ አገልግሎት ያለምንም አድልኦ ለሁሉም ዜጎች የሚሰጥ ስለሆነ ፖሊስ ከየትኛውም የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በፖሊሳዊ ሳይንስ ብቻ እንዲሰራ እና ፕሮፌሽናሊዝም እንዲጎለብት ያደርጋሉ። ፖሊስ ሳይንሳዊ ሙያ እንደ መሆኑ ሁሉ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና በወሰዱ የፖሊስ አባላት የፖሊስ ተቋማት ይመራሉ ።

ስለዚህ በፖሊስ ስልጠና ባልወሰዱ ግለሰቦች የሚመራ የፖሊስ የኦፕሬሽን ተቋም በሀገሪቱ ዐይኖርም ፤ በዚህ ዶክትሪንም የተከለከለ ነው። ፖሊሳዊ ተግባራትና የተለያዩ ኦፕሬሽኖች በፖሊስ ሙያተኞች ብቻ እንዲሰሩ ይደረጋል። ይህም ማንኛውም የፖሊስ ስራ ሙያው ባለው የፖሊስ አባል የተመራ ስለመሆኑ ዋስትናን ሲሰጥ የኦፕሬሽኑን ህጋዊነት ያረጋግጣል ።

ፖሊስ በማንኛውም ጊዜ ተግባሩን ሲያከናውን በህግ በተሰጠው የስልጣን ገደብ ውስጥ ሆኖ ሲሆን በአካባቢው መስተዳድርም ሆነ በሌሎች ተቋማት ተፅዕኖ ስር ሊወድቅ አይገባም። የፖሊስ ሙያና ተቋማዊ ነፃነት በየትኛውም ደረጃ ባለ የመስተዳድር አካል በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ህጋዊ ተቋማትና የጸጥታ ሀይሎች ዘንድ የተከበረ ይሆናል። የፖሊስ ተቋም ኃላፊዎችና አባላትም የተቋሙን ሙያዊ ነፃነት በማስጠበቅ በኩል ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ።

### 4.3.3. የፖሊስ ተቋማት ከፍትህና የዳኝነት አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፤

ፖሊስ ለወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውጤታማነት ከፍትህና የዳኝነት አካላት ጋር በህግና በትብብር በመስራት ለአገራችን ሰላምና ፍትህ መረጋገጥ ጉልህ ድርሻ ይወጣል።ፖሊስ በየትኛውም ደረጃ ከሚገኙ የፍትህና የዳኝነት አካላት የሚሰጡትን ትዕዛዛት ህግን ብቻ መሰረት በማድረግ ይፈፅማል።

ፖሊስ የወንጀል መከላከልም ሆነ ምርመራ ስራውን ያለፍትህና የዳኝነት አካላት ጣልቃ ገብነት በህግና በሙያ እየተመራ ይፈፅማል። የፍትህና የዳኝነት ተቋማት ፖሊስ መደበኛ ስራውን በህግ እየተመራ የሚፈፅም፣ ለህግ መከበርና ፍትህ መስፈን ጉልህ ድርሻ የሚጫወት እንዲሆን ተገቢ የሆነ ድጋፍና ትብብር ያደርጋሉ። ጠንካራ አገራዊ የፖሊስ ተቋም እንዲገነባ የበኩላቸውን ተቋማዊ ሃላፊነትም ይወጣሉ።

### 4.3.4. የፖሊስ ተቋማት ከሌሎች የፀጥታ አካላትጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፤

የኢትዮጵያ ፖሊስ ተቋማት ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ ከአገር መከላከያ ሰራዊት፣ የደህንነትና ሌሎች የህግ አስከባሪ አካላት ጋር በትብብርና በጋራ ይሰራሉ። ከእነዚህ ተቋማት ጋር የሚኖረው ትብብርና ግንኙነት ግልጽና ተጠያቂነትን ያመላከቱ ህጋዊ አሰራሮችንና ተቋማዊ ነፃነትን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

ፖሊስ ከእነዚህ ተቋማት ጋር የሚያከናውናቸው ተግባራት ለሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ትኩረት በሚሰጥ መልኩ ቅንጅታዊ ስራውም የህዝቡን ድጋፍ እና እምነት በሚያሳድግና በሚያጠናከር እንዲሁም የህግ የበላይነትን በሚያከብር መልኩ ይሆናሉ።

ፖሊስ የግል የጥበቃ ተቋማት (ኤጀንሲዎች) ለስራው አጋዥ እንዲሆኑ ጠንካራ የቁጥጥር፣ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት በጋራና በትብብር ይሰራል። ፖሊስ የግል የጥበቃ ተቋማት (ኤጀንሲዎች) የሞያ ብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ሳይወሰን ለወንጀል መከላከል ስራ አጋዥ በሚሆን መልኩ ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር ማድረግን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

### 4.3.5. ፖሊስ ከውጭ አገራትና አለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅቶች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፤

የኢፌዲሪ ፖሊስ ዓለም የደረሰበትን የፖሊስ ጥበብና አገልግሎት ለማስገባት ፤ ደረጃውን የጠበቀ የፖሊስ አገልገሎት ለህብረተሰባችን ለመስጠት ከሌሎች አገሮች የፖሊስ ተቋማትና አለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅቶች ጋር በትብብርና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ይሰራል። ይህ ግንኙነት የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅም፣ ሉዓላዊነት፣ የህዝቦችን ብዝሃነት፣ ባህልና እሴቶች በጠበቀ መልኩ የሚፈፀም ይሆናል።

የኢፌዲሪ ፖሊስ ከአጎራባች አገራት ፖሊስ ተቋማት ጋር ለጋራ ሰላምና ፀጥታ መረጋገጥ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል። በዚህ ግንኙነት ፖሊስ ሁሌም የሰላም ምልክት ሆኖ የሰው ልጆች በሙሉ ተፈጥሮአዊ የሆነው ሰብዓዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩና ያለስጋት ወጥተው እንዲገቡ ያለውን ቁርጠኝነት እስከ ህይወት መስዋትነት ጭምር በመክፈል ያረጋግጣል።

ኢትዮጵያ ከአጎራባች አገሮች ፖሊስ ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች የአፍሪካ እና ከዓለም አገራት የፖሊስ ተቋማት ጋር በትምህርትና ስልጠና፣ በጥናትና ምርምር እንዲሁም በሰው ኃይል ልማትና ቴክኖሎጂ  ሽግግር የሚኖራት ግንኙነት በአጋርነት ላይ የተመሰረተ ትብብር ሆኖ የአገራችንን ፖሊስ ሁለንተናዊ ተቋማዊ አቅም በሚያሳድግ መልኩ ይሆናል።

ከውጭ የፖሊስ ተቋማት ጋር የሚኖረን ግንኙነትና ትብብር ፍልስፍና ዘመናዊና የተደራጀ የፖሊስ ተቋም የገነቡ አገራትን  ልምድ በመቀመር የሀገራችንን ፖሊስ መለወጥን ፤ ማሳደግንና ማጠናከርን ዓላማ ያደረገ ይሆናል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ በመሆኗ ከሌሎች የአፍሪካና ዓለም አገራት ፖሊስ ተቋማት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ይህንን ታሳቢ ያደረገ እንዲሁም ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ እና የዓለም ህዝቦች ውክልና ያላቸውን ተቋማት ለማገልገል የሚያስችለንን ተቋማዊ አቅም ለመገንባት ጠንካራ መሰረት የሚጥል ይሆናል።

## 4.3.6. የኢትዮጵያ ፖሊስ የመገናኛ ብዙኀን አጠቃቀም፣

የመገናኛ ብዙኀን አሁን ዓለም ከደረሰበት የሉላዊነት ዘመን አኳያ የህዝብን የደህንነት ስሜት ለማሳደግ፤ ስርዓትንና የህግ የበላይነትን ለማስፈን ጠቃሚ የፖሊስ መሳሪያዎች ናቸው። ይህም ዕለት በዕለት ለሚካሄዱ የወንጀል መከላከልና ምርመራ ስራዎች ደጋፊ ናቸው ማለት ነው። ከፍተኛ የሆኑ አደጋዎችና ወንጀሎች ሲከሰቱ ህይወትን ለማዳን፤ አደጋውን ለመቆጣጠርና የህዝብን የደህንነት ግንዛቤ ለማሳደግ ይረዳሉ።

በፖሊስ መገናኛ ብዙኀን የሚሰጡ መረጃዎችና የብዙሀን መገናኛ አጠቃቀም መሰረት የሚያደርገው በአንድ ድንገተኛ በሆነ ክስተት ውስጥ የሚፈጸሙ አደጋዎችን፤ የወንጀል ክስተቶችንና ስጋቶችን ለህዝብ በቀጥታ እንዲደርሱ በማድረግ ህዝብ ከፖሊስ ተቋማት በሚለቀቁ መረጃዎች ላይ ግንዛቤውን መሰረት እንዲያደርግ ነው። በደረሱት ክስተቶች ላይ የሚተላለፈው መረጃ የህዝቡን ፍላጎት ካላሟላ በመረጃ ክፍተት ምክንያት ብቻ በፖሊስና ማህበረሰብ መካከል አለመተማመንን ያስከትላል።

በእውነተኛ መረጃ ላይ ያልተመሰረተ የፖሊስ መረጃ ለሀሜት ያጋልጣል። በጉዳቱ ችግር የደረሰባቸውም ምን ማደረግ እንዳለባቸው ዘዴዎችን ለማመንጨትና ከችግር መውጫ መንገዶችን ለመተለም ይቸገራሉ። በዚህም ህዝቡ  ሌሎች የመረጃ ምንጭ የሆኑ መስመሮችን እንደአማራጭ ለማየት ይገደዳል። ትክክለኛ የመገናኛ ብዙኀን አጠቃቀም በዚህ ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ የመረጃ

ክፍተቶችን ለማስቀረትና፤ በመገናኛ ብዙሀን የሚተላለፉ መረጃዎችን አቀራረብ፣ ዕድገት፤ ዘይቤና ተአማኒነት ለመቆጣጠር ይረዳሉ የሚለው መስማሚያ ሀሳብ በፖሊስ የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም ላይ መሰረት ይሆናሉ ።

በጣም ከባድ ወይም ከፍተኛ በሆኑ አደጋዎችና ወንጀሎች፤ ለቁሳዊና ሰብአዊ ኪሳራ ስለዳረጉ ክስተቶች፤ በክስተቶቹ ምክንያት ለጉዳት ለተዳረጉ የማህበረሰብ ክፍሎችና በአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ጥንቃቄና ኃላፊነት በመውሰድ መረጃን ለህዝብ ማድረስ የትኩረት አቅጣጫዎቹ ይሆናሉ።

በፖሊስና ሌሎች የመገናኛ ብዙኀን የሚተላለፉ ፖሊሳዊ መረጃዎች የህዝብን የደህንነት ስሜት የሚያሳድጉ፤ የወንጀል ስጋትን የሚቀንሱ፤ በፖሊስ ስራና ስኬታማነት ላይ የሚያጠነጥኑ ግቦች ላይ የሚያተኩሩ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህ ዶክትሪን በፖሊስ የምርመራ ሂደት ላይ ያሉ ሪፖርቶችና ያልተጠናቀቁ ምርመራዎች እስኪጠናቀቁ ድረስ በመገናኛ ብዙኀን እንዲሰራጩ አይፈቀድም።

በሌላ በኩል የፖሊስ መገናኛ ብዙኀን ፖሊሳዊ ባህልንና እሴቶችን (Police Culture) የሚያጎለብቱ፣ መርሆዎችን የሚያዳብሩና አባሉንና ህብረተሰቡን የሚያስተሳስሩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይደረጋሉ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ነጥቦች በፖሊስ የመገናኛ ብዙኀን አጠቃቀም ላይ ግልጽነትንና ተአማኒነት እንዲኖር ይረዳሉ። አፈጻጸማቸውም በዚህ መሰረት የተቃኘ እንዲሆን ያደርጋል ። (ዝርዝሩ በህግና ስታንዳርድ ይወሰናል።)

## 4.4. የፖሊስ ተቋማት ፖሊሳዊ ተግባራት፣ የመሰረታዊ ግብዓቶችና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ዶክትሪን

### 4.4.1. የፖሊስ የዕለት ከዕለት ፖሊሳዊ አሰራር፣

የፖሊስ ተቋም የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ለ24 ሰዓታት እና በሳምንት ለ7 ቀናት የመጠበቅና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። በመሆኑም የፖሊስ የዕለት ከዕለት ተቀዳሚ ተግባር መነሻው ማህበረሰብን እና ንብረትን ከማንኛውም አደጋ መጠበቅ ነው።

የፖሊስ ዕለታዊ ስራዎች መነሻ ህግን ማስከበር፣ ወንጀልን መቆጣጠርና ማህበራዊ አገልግሎት መስጠት ናቸው። ማህበራዊ አገልግሎቱ ከዴሞክራቲክ እና ከኮምዩነቲ ፖሊሲንግ ፍልስፍናዎች በተቀዱ ስትራቴጂዎች ለወንጀል መከሰት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ማለትም ድህነትን፣ወጣት ጥፋተኛነትን፣ ለአደገኛ ዕጽዋቶችና አፍዛዥና አደንዛዥ መድህኒቶችንና ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ችግሮች በመፍታት ላይ ያተኩራል።

በፖሊስ ዕለታዊ የስራ ክንውን የፖሊስ አባላት ፖሊሳዊ ስብዕናቸውን ሊገልጽ በሚችል አለባበስ ለተልዕኮው ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ስታንዳርድ ግብዓቶችን ይዘው ይገኛሉ። የፖሊስ የደንብ ልብስ አስፈላጊነት የፖሊስ መለያዎችና ስያሜዎች በራሳቸው የወንጀል መከሰትን ይከላከላሉ ከሚለው መሰረታዊ ፖሊሳዊ አስተሳሰብ የመነጨ ነው።

## 4.4.2. የፖሊስ የኃይል አጠቃቀም፣

በማንኛውም የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ ወቅት መግባባት፣ መደራደርና ማሳመን ቁልፍ የዕለት ከዕለት ተግባራት ማስፈፀሚያ መሳሪያዎች ይሆናሉ። የፖሊስ የኃይል አጠቃቀም የህጋዊነት፣ አስፈላጊነት፣ የተመጣጣኝነትና የተጠያቂነትን መርህ የሚከተል ሆኖ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥንና ፍትህን ማስፈንን ዓላማ ያደረገና የሰዎችን ሰብዓዊ መብት በእጅጉ ባከበረ መልኩ የሚፈጸም ወሳኝ የፖሊስ ስራ ነው ።

ፖሊስ ኃይልን የሚጠቀመው በራሱና በሌሎች ሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ጉዳት ህይወትን የሚጠይቅና በአካልም ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን ሲረዳና የመረጣቸው አማራጮች ውጤታማ ሳይሆኑ ሲቀር ብቻ መሆን አለበት ። የፌደራልና የክልል ፖሊስ ተቋማት አላስፈላጊ የኃይል አጠቃቀምን ለማስቀረት ወደ ኦፕሬሽን የሚሰማሩ የፖሊስ አመራሮችና አባላት ተገቢውን ሎጂስቲክስ አሟልተው እንዲሰማሩ የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን ባለማድረግ በሚወሰድ አላስፈላጊና ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል ተጠያቂነት አለባቸው።

በፖሊስ የኃይል አጠቃቀም ላይ ለሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥና የዜጎችን አቤቱታ የሚያዳምጥ ልዩ ቦርድም ይቋቋማል ። አሰራሩም በግልጽ ህጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የሚፈጸም ይሆናል።

## 4.4.3. የፖሊስ ስራ ማስፈፀሚያ መሰረታዊ ግብዓቶች አቅርቦትና አጠቃቀም፣

የፖሊስ ስራ ማስፈፀሚያ ግብዓቶች በወንጀል መከላከል፣ በወንጀል ምርመራና የትራፊክ ቁጥጥር የሚሰጡ አገልግሎቶች ፈጣን ቀልጣፋና ምጡቅ እንዲሆኑ አስፈላጊ ናቸው። እነዚህ ግብዓቶች ለላቀ ፖሊሳዊ አገልግሎት የሚውሉ የፖሊስ አባላት በግል እና በጋራ ጥቅም ላይ ሊያውሏቸው የሚገቡ ናቸው።

እነዚህ ግብዓቶች የፖሊስ ተቋም የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ለማድረግ፣ የተቋሙን ገፅታ (Image) ለመገንባት፣ፖሊስ በህዝቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና ተአማኒነት ለማሳደግ፣ የፖሊሳዊ ሙያን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር፣ ሰብዓዊ መብቶችን በተገቢ ሁኔታ ለማስከበር፣ እንዲሁም የኃይል እርምጃ በሚወስድበት ወቅት ሊደርስ የሚችለዉን አደጋ ወይም ኪሳራ ለመቀነስ የሚያስችሉ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም ግብዓቶቹ የፖሊስ አመራርና አባላት በራስ የመተማመን አስተሳሰባቸውን ለማበልፀግ እንዲችሉና ጤናማ የአካልና የአእምሮ ብቃት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ መሆናቸው ታሳቢ ተደርጎ መቅረብ አለባቸው። የፖሊስ ስራ ማስፈፀሚያ ግብዓቶች የአቅርቦት፣ የአጠቃቀም እና የአሰራር ዕሳቤ የፖሊስን ስራ ቀልጣፋ ፈጣንና ውጤታማ ማድረግ ይሆናል።

በፖሊስ አልባሳት እና የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት መገልገያዎችና ሌሎች ልዩ ልዩ መገልገያዎች ላይ ማህበረሰቡ በቀላሉ የሚለያቸው ቋሚና ዘለቄታነት ያላቸው ቀለማት፣ አርማዎች (Logos) ፣ ፅሁፎች እና የመሳሰሉት ፖሊሳዊ መለያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም የፖሊስ አባላት ማንነታቸውን የሚገልጹ ዲጅታል መታወቂያ እና መለያ ቁጥር ይኖራቸዋል።

አባላት ፖሊሳዊ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት በማንኛውም ወቅት ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መለያዎችን ለማህበረሰቡ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ በደረታቸው ላይ የማንጠልጠል ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ የፖሊስ መገለጫ የሆኑ መለያዎች ከፖሊስ ተቋማትና አባላት ውጭ ማንኛውም ግለሰብም ሆኖ ተቋም እንዳይጠቀምባቸው የህግ ድጋፍና ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

ከላይ የተመለከቱትን አስተሳሰቦች ተግባራዊ ለማድረግ የፖሊስ ስራ ማስፈፀሚያ ግብዓቶች በተገቢው መጠንና ዓይነት ተሟልተው፤ ወቅታቸውን እና ጥራታቸዉን ጠብቀው በግልጽ ስታንዳርድ ይቀርባሉ፤ ጥቅምም ላይ ይውላሉ።

## 4.4.4. የፖሊስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖለጂ (ICT) አቅርቦት እና አጠቃቀም፣

የፖሊስ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ግብዓቶች ማለት ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመመርመር እና የትራፊክ ቁጥጥርንና ደንብን ለማስከበር ፖሊስን የሚረዱ አጋዥ እና ማሳለጫ ግብአቶች ማለት ናቸው።

በአጠቃላይ የላቀ ፖሊሳዊ አገልግሎት በወቅቱ፣ በጥራትና በተደራሽነት ማህበረሰቡ በሚፈልገው ደረጃና ብቃት ለመስጠት የሚያስችሉ ሆነው መረጃን ወይም ዳታን ለመሰብሰብ፣ ለማጠራቀም፣ ለማግኘት፣ ለማደራጀት፣ ለመተንተን፣ ለመጠቀም እና ለማሰራጨት ጥቅም ላይ የሚዉሉ ዘመኑ የወለዳቸው ግብዓቶች ማለት ናቸው።

የፖሊስ ኢንፎርሜሽን አገልግሎት የማቅረብና የመጠቀም መነሻው ሀሳብ የፖሊስን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ማሳደግ ሲሆን ለተለያዩ የፖሊስ አገልግሎቶች ለሚቀርቡ ጥሪዎች የሚሰጡ ምላሾች ፈጣን፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። በተለይም የፖሊስ ቴክኖሎጂ ከዘመኑ ጋር ተለዋዋጭ፣ አጠቃቀሙም ከሀገር ሉዓላዊነት ጋር በቀጥታ የተገናኘ በመሆኑ በዋናነት በተቋሙ ውስጥ የቴክኖሎጂ ፈጠራ እና የራስ አቅም ማጎልበትን የሚያበረታቱ ስርዓቶች ይዘረጋሉ።

ይህ ዶክትሪን የፖሊስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በዜጎች ማንነት ላይ የሚደረጉ ማናቸውንም ዓይነት ስለላዎችን በፍጹም አይፈቅድም። ተቋሙንና አገልግሎቱን በላቀ የፖሊስ ቴክኖሎጂ መደገፍ ዋናው እሳቤ ወይም የፍልስፍናው መነሻ በ21ኛው ክ/ዘመን ላይ የሚታዩና ተለዋዋጭ ባህሪይ ያላቸውን ወንጀሎችን በብቃት ለመከላከል እንዲቻለው በማብቃት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ነው።

ከዚህ አንፃር የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ አቅም እና ማህበረሰባዊ ዕድገት ባገናዘበ መልኩ ማናቸውም የፖሊስ ተግባራት በአስፈላጊ እና ዘመኑ በደረሰበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) እንዲደገፉ

ይደረጋል። በተለይም በፖሊስ ምርመራ የሚገኙ መረጃዎች እና ውጤቶች ተአማኒ እና ፍትሃዊ እንዲሆኑ እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶች በተገቢው መንገድ እንዲከበሩ ከተለመደው የአናሎግ አሰራር እና የሰው ማስረጃ ጥገኝነት በመላቀቅ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) እንዲደገፉ ይደረጋል። በዚህም የፎረንሲክ ምርመራዎችን በተገቢው ቴክኖሎጂ በማዘመንና የባለሙያዎችን እውቀትና ክህሎት በማጎልበት በዚሁ ምርመራ የሚገኙ ውጤቶች እንዲሁም ሙያዊ ምስክርነትና ማረጋገጫዎች በፍትህ ስርዓቱ የሚኖራቸው ተቀባይነት አስተማማኝ እንዲሆን ይደረጋል።

በአጠቃላይ በፖሊስ ውስጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ጥቅም ላይ የሚውለው ብቃት ያለው የፖሊስ አገልግሎት ለመስጠትና ተደራሽ ለማድረግ፣ የሰውን ህይወት ከአደጋ ለማዳንና ለመጠበቅ ነው። የሚቀርበው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከህብረተሰቡ እና በተቋሙ ውስጥ የሚደረግ ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥን ለማሳለጥ፣ የውስጥ አሰራርን ለማዘመንና ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ፣ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት (Central Data Base) ለማጠናከር እና ከዚሁ ጋር ተጓዳኝ ለሆኑ ለታወቁ እና ግልፅ ለሆኑ ተግባራት ብቻ ይውላል። በዚህ አስተሳሰብ መነሻ የፖሊስ ኢፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ከወቅቱና አዳጊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው በግልጽ ስታንዳርድ የሚመሩ እና የሚፈጸሙ ይሆናል።

# ክፍል አምስት

## ማጠቃለያ

የኢፌዴሪ ፖሊስ ዶክትሪን በኢፌዴሪ ህገ መንግስት ውስጥ የተደነገጉ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና አለም አቀፍ ስምምነቶችን ቀምሮ የያዘ የአስተሳሰብና ስምምነት ሰነድ ነው። የዶክትሪኑ መኖር ነጻ፣ ገለልተኛና ህዝባዊ መሰረት ያለው የፖሊስ ተቋምንና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግም ይረዳል። በፖሊስና ህዝብ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠርና በህዝብ ይሁንታ የሚሰራ ተቋም እንዲሆንም ይረዳል። ከፍልስፍናና ስምምነት በተጨማሪም ሌሎች ህጎች፣ ማቋቋሚያ አዋጆች፣ ስታንዳርዶች፣ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች መሰረት ሲሆን ወጥ ተቀራራቢና ደረጃውን የጠበቀ የፖሊስ አገልግሎትን መሰረትን ለማስያዝም ይረዳል።

የዶክትሪኑ ተፈጻሚነት በኢፌዲሪ የግዛት ወሰን ውስጥ ባሉ የፖሊስ ተቋማት ላይ ሁሉ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የፖሊስ አገልግሎት ተቀራራቢ፣ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ፤ በመርህ የሚመራና ፣ በትውልዶች ቅብብሎሽ እየተገነባ የሚሄድ እንዲሆን ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ፖሊስ የራሱ ፍልስፍናና የጋራ እሴቶች የሚመራ እንዲሆን ለማድረግ ቅኝቱን የሚዘውር ዶክትሪን ማውጣት ከምንም በላይ ቀዳሚ የሆነ ስራ መሆን እንዳለበት ስምምነት ላይም ተደርሷል፡ ፡ ይህ እሳቤ የሌሎች ሀገራትን ልምድ የሚጋራ ሲሆን የዶክትሪኑ መኖር በዓላማው ላይ ከተጠቀሱት አንጻራዊ ጥቅሞች በተጨማሪ አለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነትንም ያረጋግጣል።

ለዚህ ዶክትሪን ዕውን መሆን ምክንያቱ በተለያየ ጊዜያት በተካሄዱ የጥናትና ምርምር ግኝቶች የተሰጡ አስተያየቶች ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ የፖሊስ ስትራቴጂክ ፍኖተ ካርታ፣ ስታንዳርዶች፣ ደንቦችና የስራ መመሪያዎችም ይገኙበታል። የፖሊስ ዶክትሪን ባለመኖሩ ምክንያት የተከሰቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችና ልዩነቶች በሰፊው ተመላክተዋል። የፖሊስን አገልግሎት አሰጣጥ የሚመራ ኢትዮጵያዊ ይዘት ያለው አስተሳሰብ ወይም ፍልስፍና አስፈላጊ መሆኑ ደግሞ ሚዛን ደፊው ነጥብ ነው።

በአጠቃላይ ዶክትሪን የለውጥ ማምጫ መሳሪያ ነው የሚለው ለዚህ ዶክትሪን መኖር አንዱ ሀሳብ ነው። በዚህ ዶክትሪን ገዥ የፖሊስ ዕሴቶች በቀላሉ የሚያዙ ተደርገው የተቀመሩ ሲሆኑ እነርሱም፡- ሙያዊ ብቃት፣ ምሉዕነት፣ ብዛሀነትንና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር ናቸው።

የሀገሪቱን ፖሊስ ከፖለቲካ ነጻ፣ አስተሳሰቡና አሰራሩ ወታደራዊ ያልሆነ፣ በአደረጃጀቱ ያልተማከለና ፍጹም ዲሞክራት የሆነ ማድረግ ደግሞ ከአደረጃጀትና አሰራር ጋር የሚሄዱ መሪ የቅኝት አቀጣጫዎች ናቸው። የአገልግሎት አሰጣጡ ህዝብን ማዕከል ባደረገ ከታች ወደ ላይ በሚሄድ (Bottom to Up) መሰረት ላይ የተደራጅ ሆኖ የኮምዮኒቲ ፖሊሲንግና ዲሞክራቲክ ፖሊሲንግ ፍልስፍናዎች ዋና ማዕከሎች ናቸው። ማህበራዊ አገልግሎትን መስጠት (Social Service)፣ ህግን ማስከበር (Law Enforcement)፣ ወንጀልን መከላከልና (Crime Preven-tion) በማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ ላይ ለውጥ በማምጣት ላይ መስራትን ያያል። በቅድመ ወንጀል መከላከል ስትራቴጂ ለወንጀል መፈጠር ምክንያት የሆኑ ችግሮችን መለየትና መፍታት እንደ አንድ ወሳኝ የፖሊስ ስራ ይወስዳል።

የፖሊስ ተቋማት ትኩረት፣ ህግጋትና አደረጃጀቶች በግልጽ ተቀምጠዋል። በክልልና የፌደራል ፖሊስ መካከል የሚኖሩ ግንኙነቶች በሀገሪቱ የፌደራል አወቃቀር ላይ መሰረት ያደረገ ሆኖ በመከባበር፣በመተማመንና በአጋርነት ላይ በተመሰረተ ግንኙነት ክልል ተሻጋሪ ወንጀሎችን መከላከል ያጠናክራል። የፖሊስ አገልግሎትም በቀዬው አጠቃላይ ስነልቦና፣ ባህሎችና ዕምነቶችን ከትኩረት ውስጥ ይወስዳል። በህዝብ ይሁንታና ተቀባይነት እንዲሁም ርካት የሚመዘንና የሚቀጥል ተቋምም ያደርገዋል። የፖሊስን ስራ የሚከታተል ልዩ የገለልተኛ አማካሪ ቡድን እስከታችኛው የማህበረሰብ አወቃቀር ድረስ ይኖረዋል። ስታንዳርዶችን ለማስፈጸምም የፌደራል ፖሊስ የኢንስፔክሽን፣ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያካሄዳል ጉባኤዎችንም ያዘጋጃል።

ከሙያዊ ነጻነቱና ገለልተኛ አደረጃጀቱ አንጻር በህዝብ ተቀባይነት ያላገኘና በህገመንግስታዊ ስርዓቱ መሰረት ወደ ስልጣን ያልመጣን መንግስት አይቀበልም። በቁጥጥር ስር አውሎም ይመረምራል፡ ፡ የመጣበትን ኢ-ህገመንግስታዊ መንገድ አጣርቶ ለህግም ያቀርባል። ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በጽናት ይጠብቃል።

የፖሊስ አባል ለመሆንና በተለያዩ የስልጣን እርከኖች ላይ ለመመመደብ ከፖሊስ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች መመረቅና ማረጋገጫ ማግኘትን ይጠይቃል። ከዚህ ውጪ የሚደረጉ ምደባዎች በዚህ ዶክትሪን

የተከለከሉ ናቸው። የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ዓላማዎች በፖሊስ ሙያ የላቀ ዕውቀት ያላቸው የፖሊስ አባላትን በማውጣት፣ የሰላም አምጪ አባት፤ የማህበረሰብን ችግር ለመፍታት የሚረዱ ለየት ያሉ ሀሳቦችን አመንጪ፤ የስነ ልቦና አማካሪና የማህበረሰብ ሳይንስ ተማራማሪ በማድረግ የዘርፈ ብዙ ዕውቀቶች ባለቤት ማድረግ ነው።

የፖሊስ ማዕረግ ምልክት ሳይሆን ተዋረድን የሚያሳይ ማዕረግ ነው። የፖሊስ ስነምግባርና ስብዕና ግንባታዎች በዚህ ዶክትሪን ትልቅ ቦታ ተሰጥቶአቸዋል። በፖሊስና ማህበረሰብ መካከል ሊኖር ስለሚገባ ግንኙነት በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን በተለይም የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግን ፍልስፍና ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ የሚረዱ የማበልጽጊያ ተቋማት በብዛት ይኖራሉ።

የኢፌዲሪ ፖሊስ የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀምና የትኩረት አቅጣጫ ትክክል የሆነ መረጃን ለህዝብ በማስተላለፍ ንቃተ ህግን ማጎልበትና ተአማኒ የሆነ የመረጃ ምንጭ እንዲሆን በማድረግ ላይ ያተኩራል፡ ፡ የፖሊስ ቴክኖሎጂ አጠቃቀሞች ለፖሊስ ስራ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ላይ ብቻ ያተኩራል። ከወንጀል ጋር ምንም ግንኙነት በሌላው ጉዳይ የሚደረግ ስለላን በዜጎች ላይ ማድረግን ይከለክላል። የፖሊስ የኃይል አጠቃቀምና ርምጃ አወሳሰድም ተመላክቷል።

በዚህ ዶክትሪን ውስጥ ያልተካተቱ ሀሳቦች በዝርዝር ህግም ይወሰናሉ። ወደ መሬት ለማውረድም በፖሊስ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ስታዳርዶች፣ መመሪዎች እና ማስፈጸሚያ ማነዋሎች የሚብራራ ሲሆን ለተፈጻሚነቱ እንዲረዳም የፖሊስ ስትራቴጂክ ፍኖተ ካርታ ይኖረዋል። ይህም የወደፊቱን የፖሊስ ዕጣ ፋንታ ይወስናል። ዘመን ተሻጋሪነቱንም ያረጋግጣል።

የሰላም ሚኒስቴር

MINISTRY OF PEACE

